

ግብረ-ገብ ትምህርት

የተማሪው መማሪያ መጽሀፍ

3ኛ ክፍል

ለመጽሐፍ መደረግ ያለበት ጥንቃቄ

ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ከመሆኑም በተጨማሪ በቀጣይ ታናናሾቻችሁ የሚማሩበት ስለሆነ መጽሐፉ እንደይቀደድ ወይም እንዳይበላሽ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህ ለጥንቃቄ ይረዳ ዘንድ የሚከተሉትን 10 ነጥቦችን ልብ በሉ።

1. የመጽሃፉን ደህንነት ለመጠበቅ በፕላስቲክ፣ በአሮጌ ጋዜጦች ወይም መጽሔቶች ሸፍናችሁ ያዙ፤
2. መፅሐፉን ሁልጊዜ ንጹህና ደረቅ በሆነ ቦታ አስቀምጡት፤
3. መጽሐፉን ስትጠቀሙ እጆቻችሁ ንጹህ መሆናቸውን አረጋግጡ፤
4. በመጽሐፉ ሽፋን ላይም ይሁን በውስጥ ገጾቹ ላይ ምንም ነገር አትጻፉ፤
5. መጽሐፉን ሲይዙ ላበት እንዳያበላሸው አንድ ወረቀት ወይም ካርቶን ይጠቀሙ፤
6. ማንኛውንም ስዕሎች ወይም ገጾች ፈጽሞ አትቅደዱ ወይም አትቁረጡ እንዲሁም የተቀደዱ ገጾች ካሉ በመለጠፍ ወይም በመጠገን ተጠቀሙ፤
7. መጽሐፉን በትምህርት ቤት ቦርሳ ውስጥ ስታስገቡም ሆነ ስታወጡ በጥንቃቄ አድርጉ፤
8. መጽሐፉን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ስትጠቀሙ በጥንቃቄ ተጠቀሙ፤
9. አዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጠቀሙ በጀርባው አስቀምጡት፤

10. **በአንድ ጊዜ ጥቂት ገጾችን ብቻ ክፈቱ፤ ገጾቹን በምትቀይሩበት ጊዜ ከታሰረው ጠርዝ ጋር ትንሽ ተጫኑ። ይህም ሽፋኑን በጥሩ ሁኔታ እንዲቆይ ያደርገዋል።.**

ፀሃፊዎች

1. **ኪዳነ ኃይሉ ደሜ** (M. ed)
2. **ማሩ ማቴዎስ እረባቶ** (M.A)

አዘጋጆች

1. **ዳኜ ጥላሁን አሰፋ** (M.A)
2. **ጃንቦ ጉዱሩ ፊጋ** (M.A)
3. **ዶ/ር እባቡ ተፈራ አዱኛ** (Associate Professor)

አስማሚዎች

1. **ንጋቷ ዛፉ** (M.A)
2. **ታዲዎስ ቦንጋ** (M.A)

የይዘት አርታኢ

- **ሳባ መንግስቱ**

የይዘት አርታኢ

- **ወዳጀነሽ አሸንጎ**

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ አጠቃላይ የሕትመት ወጪው ተሸፍኖ ሲሆን፤ በኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴርና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እንዲሁም በአርባምንጭ ትምህርት ኮሌጅ የቴክኒክ ድጋፍ በ አማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቷል።

የመጽሐፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው።

መግቢያ

ሰዎች ማህበራዊ እና ምክንያታዊ እንስሳ ናቸው፡፡ በብዙ መልኩ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ በባህሪው ይገለጻል። ባህሪ ያለው የሰው ልጅ ብቻ ነው። ባህሪ በሰዎች የሚገነባው ለራሳቸው ያቀዱትን አላማ ለማሳካት እራሳቸውን ፍጹም ማድረግ እስከቻሉ ድረስ ነው። ባህሪን ለማግኘት የሰው ልጅ ከምክንያት እና ሥነ ምግባር የሚመነጩ የተግባር መርሆች እንዲኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ባህሪ ሌሎችን በመምሰል አይፈጠርም ምክንያቱም የሰው ልጅ ባህሪ በራሱ አስተሳሰብ እንደሚመራ ይታሰባልና፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ በምድር ላይ ካሉ ፍጥረታት ጋር ሲወዳደር ልዩነቱ የምክንያትና የህሊና መኖር ነው። በርግጥም የሰው ልጅ የሞራል ግዴታዎችን የመወጣት አቅም ወይም ችሎታ አለው።

ግብረ ገብ ውስብስብ በሆነ ዓለም ውስጥ እንዴት አብረን መኖር እንዳለብን አስቻይ እውነታን መፈለግ እና መረዳት ነው። በተጨማሪም, የማህበራዊ ህልውና ቁጥጥር አይነት ነው፡፡ እያንዳዱ ማህበረሰብ መደበኛ፣ ትክክለኛ ወይም የሚጠበቁ የባህሪ መንገዶችን በራሳቸው ይገልፃሉ። ስለዚህ፣ እነዚህ የሚጠበቁ ባህርያት ህብረተሰቡ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲሠራ የሚያግዙ የባህሪ መመሪያዎች ሆነው የሚያገለግሉ ማህበራዊ ደንቦች ናቸው። ማንኛውም ህብረተሰብ ቀጣይነት እንዲኖረዉ ከተፈለገ ማህበራዊ ደንቦቹን እና ወጎቹን ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ማስተላለፍ መቻል አለበት፣ምክንያቱም

ሰዎች እስካልተማሩ ድረስ ከማህበራዊ ደንቦች ጋር መግባባት እና መስማማት እንደማይችሉ ሀቅ ነው። በርግጥም ሰዎች ማህበራዊ ደንቦችን የሚማሩት በሞራል አስገዳጅነት ነው። በሌላ አነጋገር፣ ሰዎች የማህበረሰባቸውን ደንቦች ሲማሩ፣ እነሱን ለመታዘዝ የሞራል አስፈላጊነትንም ወደ ውስጣቸዉ ያዋህዳሉ። ለዚህም ነዉ ደንብ በሰዎች ልማድ ወይም አኗኗር ውስጥ የተካተተ የዕለት ተዕለት ተግባር የሚሆነዉ። ማድረግ ያለብንን ወይም ማድረግ የሌለብንን የሚደነግገው የህብረተሰቡ የባህሪ መመሪያ (የህብረተሰቡ የስነ ምግባር መመሪያ) ነው።

ግብረ ገብ የደንቦች ስብስብ ማዕቀፍ ነዉ። እነዚህ ደንቦች ነፃነታችንን የሚገድቡ ቢሆኑም በትክክል መከተል አለብን። በአጠቃላይ ግብረ ገብ እነዚህ አምስት ዓላማዎችን ይዟል። የህብረተሰቡ ትስስር እንዳይፈርስ መጠበቅ፣የሰዎችን ስቃይ መቀነስ፣የሰው ልጅ እድገትን ማበረታታት፣የጥቅም ግጭቶችን በፍትሃዊነትና በስርዓት መፍታትና ምስጋና እና ወቀሳ፣ ሽልማት እና ቅጣት፣ እና ጥፋተኝነትን መወሰን የሚለውን ይይዛል።

ግብረ ገብ በማህበራዊ ደረጃ ከጥንቃቄ ጋር ይመሳሰላል። በሌላ አገላለጽ ግብረ ገብ የጋራ ግቦቻችን ላይ እንድንደርስ ለማስቻል የተቀመጡ ደንቦች ወይም ወጎች ስብስብ ነው።

ዛሬ የግብረ ገብ ትምህርት ለሰው ልጅ ሕልውና እና እድገት አስፈላጊ ነው። ነፃና እንደሰለጠነ ህዝብ ሆነን መጽናት ካለብን ከዚህ በፊት ከነበረው ይልቅ የሞራል እሴቶችን በትኩረት ልንመለከት ይገባል። ግብረ ገብነት ጥሩ ሕይወት ለማግኘት እና ለመኖር የሚደረግ ጥረት

ነው። በእርግጥ ሰዎች አሁንም የሞራል ደንቦች ወይም መርሆዎች አሏቸው። ነገር ግን፣ እነሱን ለመታዘዝ ራሳቸውን የመስጠት ፍላጎት ካላሳዩ በስተቀር እነዚህ ደንቦች እና መርሆዎች ብቻ የሞራል ባህሪን ሊያረጋግጡ አይችሉም። በዚህ ምክንያት የግብረ ገብ ትምህርት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ዛሬ አስፈላጊ ነው። የሞራል እሴቶችን እና መለኪያዎችን ከራሳችን ጋር ማዋሀድ ከቻልን ኢሰብአዊ ድርጊቶችን፣ ጭካኔዎችን እና ክፋቶችን መቀነስ እንችላለን። የግብረ ገብ ትምህርት ደንቦችን ማስተማር የመልካም ባህርያትን የታማኝነት፣ ራስን መግዛትን፣ ድፍረትን፣ ወዳጅነትን፣ ትሕትናን፣ ክብርን፣ መከባበርን እና መቻቻልን ማዳበር ነው። በተጨማሪም ልጆች በተናጥል ጥሩ ሕይወት እንዲኖሩ፣ በሰላማዊ መንገድ ከሌሎች ጋር እንዲገናኙ እና በተመሳሳይ ጊዜ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚረዳቸውን በጎ ምግባር ወይም ሥነ ምግባራዊ ልማዶች እንዲይዙ መርዳትን ይመለከታል። ተማሪዎች ከሌሎች ጋር በሰላም አብረው እንዲኖሩ የሚያግዙ የግብረ ገብ እሴቶችን ጠንቅቀው ይገነዘቡበታል የግብረ ገብ ትምህርት የተማሪዎችን ማኅበራዊ እና ሥነ ምግባራዊ እድገት ያረጋግጣል።

በኢትዮጵያ የግበረ ገብ ትምህርት አዲስ ክስተት አይደለም። ትምህርቱ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ እንደተጀመረ በተለያዩ ጥናቶች የተረጋገጡ በቂ ማስረጃዎች አሉ። ይሁን እንጅ የትምህርቱ ይዘቶች ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ጋር የወገናዊነት ዝንባሌ እንደነበራቸዉ ይታመናል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አሁን ያለው ሥርዓተ-ትምህርት-ተኮር የግብረ ገብ ትምህርት በዋናነት ዓላማው ትምህርቱ በተማሪዎች ላይ የባህሪ እና የአመለካከት ለውጥ እንድያመጣ ታስቦ ተዘጋጅቷል። ከዚህ በተጨማሪ

ሥርዓተ ትምህርቱ ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎችን ለማፍራት የተነደፈ ነው። ትምህርቱን በተቻለ መጠን ኢትዮጵያዊ ለማድረግ የተቀናጀ ጥረት ተደርጓል። በአዲሱ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ የግብረ ገብ ትምህርት ከ1-6ኛ ክፍል እንደ ዋና ትምህርት እንደሚሰጥ በግልፅ ተቀምጧል። በተለይም የ3ኛ ክፍል የግብረ ገብ ትምህርት የተለያዩ ይዘቶችን ይዟል፡ ሰብዓዊነትን ማክበር፣ ሌሎችን ሰዎች ማክበርን፣ እኩልነትን፣ ባህልን ማክበር ፣ ሰላም፣ ትብብር፣ እና ባህለ- ብዝሃነት ከይዘቱ ጥቂቶቹ ናቸው። በአጠቃላይ አሁን ያለው የሥርዓተ-ትምህርት-ተኮር የግብረ ገብ ትምህርት ተማሪዎች ክህሎቶችን፣ ዕውቀቶችን፣ አመለካከቶችን እና እሴቶችን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። በተለይም የ3ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ከስርአተ ትምህርቱ አንፃር ተጽፏል።

ትምህርቱን ከማዳረስ አንፃር የመምህሩ ሚና ከሁሉም ነገሮች የላቀ መሆን አለበት። በተለይም ትምህርቱን ሳቢ በሆነ አቀራረብ ከማድረስ አንፃር መምህሩ አሳታፍ የማስተማር ስነ ዜደን መጠቀም አለበት፡፡በእያንዳንዱ ርዕስ ውስጥ የተቀመጡት የክፍል ዉስጥ ተግባራት ለዚህ አላማ በጣም አጋዥ ናቸው። በመሆኑም ተማሪዎቹ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የመማር ሂደቱን ተግባራዊ ካደረጉ እንዲሁም የፈጠራ ችሎታቸውን ከተጠቀሙ የክፍል ደረጃዉን ግቦች በጥሩ ሁኔታ ያሳካሉ፡፡

ምዕራፍ አንድ

ሰብዓዊነትን ማክበር

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፡

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፣

- የሰብዓዊነትን ትርጉም መግለፅ ትችላላችሁ፣
- የሰብዓዊነትን መሰረታዊ በህሪያት ትገልጻላችሁ፣
- የሰዎችን ሰብዓዊ ክብር መጠበቅ ስለሚያስገኘው ጠቀሜታ ዋጋ ትሰጣላችሁ፣
- የሰው ልጅን መሰረታዊ ባህሪያት ታውቃላችሁ፣
- የሰብዓዊ ክብር አለመኖር የሚያስከትለውን ጉዳት ትለያላቹ፡፡

በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች

1.1 ሰብዓዊነት

1.2 የሰው ልጅ ክብር

1.2.1. ሰውን የማክበር አስፈላጊነት

1.3. መሰረታዊ የሰው ልጅ ባህሪያት

መታወስ የሚገባቸው ቁልፍ ቃላት፡

ደግነት ክብር ርህራሄ ፍርድ

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የሰብዓዊነትን ትርጉም ያስተዋውቃል በተጨማሪም ስለ ሰብዓዊ ክብር አስፈላጊነት ግንዛቤ ይፈጥራል። እንዲሁም የሰዎችን ሰብዓዊ ክብር ማክበር ሰለሚየስገኘው ጠቀሜታ ያስረዳል ። በተጨማሪም በምዕራፉ በሰፊው የሚዳሰሱ ሀሳቦች ደግሞ እንደ ፍቅር፣ ርህራሄ፣ በጎነት፣ ጨዋነት ፣ ወንድማማችነት ፣ ትዕግስት እና ሰላም ናቸው። በመጨረሻም የሰውን ልጅ ክቡርነት አለማረጋገጥ የሚያስከትለውን መዘዝ እና የሰው ልጅን መሰረታዊ ባህሪያትን በሰፊው ያብራራል።

ሰብዓዊነት

ሰብዓዊነት የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ በቀላሉ ለመግለጽ አዳጋች ነው። ሆኖም ሰብዓዊነትን በሁለት መንገድ ልንገነዘበው እንችላለን። የመጀመሪያው የሚገልፀው የሰውን ተፈጥሮ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሰውን ልጅ ባህሪ ያመለክታል። ከዚህ በማስከተል ከለይ ሰለጠቀስናቸው ሁለት ሃሳቦች በሰፊው እንወያያለን።

ሀ. የሰው ልጅ

የማነቃቂያ ጥያቄ

ከዚህ በታች የቀረበውን ምስል በመመልከት የሰው ልጅ የሆነውን ለዩ?



ምስል 1.1 እንስሳ ፤ የሰው ልጅ እና ቁስ

ተግባር 1.1

1. **ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎች በሚከተሉት ቃላት ወይም ሀረጎች ሙሉ።፡**

ምስል ሀ----------ያሰያል የሰውን ልጅ

ምስል ለ----------ያሳያል እንስሳ

ምስል ሐ----------ያሰያል መፅሐፍ

2. ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት በሰው ልጅ እና በሌሎች እንስሳት መካከል ወይም በሌሎች ቁሳዊ ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት ተወያዩ?
3. የተወያያችሁበትን የቡድን ሐሳብ ለሌሎች ቡድኖች አካፍሉ?

ሰብአዊነት የሰውን ዘር ወይም የሰው ልጅን የሚያመለክት ሲሆን ቃሉ የመጣው ሰው ከሚለው ዋና ቃል ነው።።የሰውን ልጅ ከሌሎች እንስሳት የተለየ የሚያደርገው የተለያዩ አቅሞች ስላሉት ነው።። ለምሳሌ።- በምክንያታዊነት ማሰብ ይችላሉ፣ ውሳኔዎችን በራሳቸው መወሰን ይችላሉ ፣ ለክብራቸው ይታገላሉ እና የሌላውን ክብር የመጠበቅ እና የማክበር ሀላፊነት አላቸው።።

በሰዎች መካከል በዘር፣በቁመት፣በጸታ፣በቋንቋ፣ወዘተ ልዩነት ቢኖርም ሰብአዊነት ሁሉንም ሰው እኩል ያደርጋል።። በመሆኑም ጓደኞቻቸሁን በኢኮኖሚ ሁኔታ ወይም በሌላ መስፈርት ማግለል የለባችሁም።። ምክንያቱም ሰብዓዊነት ያለምንም መድሎ እና መገለል የሰው ልጆች እኩል እንደሆኑ ያረጋግጣል።።

ለ. የደግነት ማሳያዎች

ቀጥሎ ክቀረበው ምስል ምን ትረዳላችሁ?



ምስል 1.2 የሰዎች መተባበር

ተግባር 1.2

ውድ መምመህር! አራት ተማሪዎችን ያቀፈ ቡድን ይመሰርቱ። ከላይ የተቀመጠውን ምስል ለተማሪዎች ካሳዩዋቸው በኋላ እጅ ለእጅ ተያይዘው እንዲተገብሩት ያድርጉ ። ከዚያም ድምጻቸዉን ከፍ አድርገዉ የሚከተሉትን ሀረጎች እነዲናገሩ ያድርጓቸው። "እኛ ሰዎች ነን!"፤ "ሰብአዊነት ደግነት ነው!" ፤ "ሰብአዊነት ትብብር ነው!" ፣ "አንተ/አንች በምትፈልገኝ ጊዜ ሁሉ እደግፍሃለሁ!"

1. ተማሪዎች ከዚህ ተግባር በኋላ ምን ተሰማችሁ?
2. በሰዎች መካከል ስለሚኖር ትብብር ያላቸሁንን ስሜት ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ?

ከላይ ከቀረበው ተግባር ስለ ሁለተኛው የሰው ልጅ ጽንሰ-ሀሳብ መማር እንችላለን፡፡ በመሆኑም እነዚህ የቅን ልብ ባለቤት የመሆን ማሳያዎች እና የጥሩ ባህሪ መገለጫዎች ናቸው ፡፡ ሰብዓዊነት ማለት እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን ያለምንም አድሎ እና መገለል መርዳት ማለት ነው፡፡ በሰብዓዊነት ሰዎችን ስናገለግል ጥሩ ጓደኝነትን ፣መግባባትን፣ አንዱ ሌላውን መርዳትን እንፈጥራለን፡፡ከዚህም በተጨማሪ መተባበር፣ሰላምን እና ጤናማ የሆነ ሕይወትን በሰዎች መካከል እንዲኖር ከማድረግም በተጨማሪ እርስ በእርስ መደጋገፍ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ተማሪዎቻችንም የቅንነትን እና የደግነትን ባህሪይ ስለሚያሳድጉ በትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ወይም በማንኛውም ቦታ አደጋ ቢደርስ ከመርዳት ወደኋላ አይሉም፡፡

1.2 የሰው ልጅ ክብር

የማነቃቂያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ከሰው ልጆች ተነጥሎ የማይታይ ነገር ልትነግሩን ትችላላችሁ?

በቀላል አነጋገር “ሰብአዊ ክብር” ማለት ለሰው ልጅ የምንሰጠው “ግምት ወይም ዋጋ” ማለት ነው።

የሰው ልጅ ክብር በእርግጠኝነት ሰው ከሚለው ጽንሰ ሃሳብ የማይለይ እና ቀጥታ ለሰው ልጅ ከምንሰጠው ግምት ወይም ዋጋ ጋር ይገናኛል ። የሰው ልጅ ከተወለደ ጀምሮ ነፃ እና እኩል ክብርና ነፃነት አለው፡፡ የሰው ልጆች ይህንን ክብር በመረዳት ከሌሎች ጋር በወንድማማችነት መንፈስ መዋድድ አለባቸው ፡፡

ተግባር 1.4.

ሰዎች ክብራቸውን በምን ምክንያት ሊያጡ ይችላሉ?

ክርክር

ቡድን ሀ (አዎ)	**ቡድን ለ (አይ)**
ሰዎች ክብራቸውን ያጣሉ ያላችሁበትን በምን ምክንያት ሊያጡ እንደሚችሉ ዘርዝሩ፡	**ሰዎች ክብራቸውን አያጡም ያላችሁበትን ምክንያት አብራሩ፡**

ምንም እንኳን ሰብዓዊ ክብር ተፈጥሮአዊ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ይህንን ክብር ለልናጣ አንችላለን፡፡ በመጀመሪያ የሰው ለጅ የራሱን ክብር የሚያጣው ለራሱ በሚሰጠው የተሳሳተ ግምት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት የሌለው ባህሪ የሚያሳይ ከሆነ እና ማህበረሰቡ አጥብቆ የሚጠላቸውን የሥነ ምግባር ችግሮች ማለትም መስረቅ፣መዋሸት፣ሙስና፣ ሰውን መግደል፣ ታማኝ አለመሆን፣ ወዘተ መጥፎ ባህሪያትን የሚያሳይ ከሆነ የሰዎችን ክብር ሊያሳጡ ይችላሉ፡፡

ተግባር 1.5

1. **በማህበረሰባችሁ ውስጥ ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው ሰዎች እነማን ናቸው። አስተዋጽአቸዉን ግለፁ?**
2. **በራሳችሁ መጥፎ ባህሪ ምክንያት ሰብዓዊ ክብርአችሁን ብታጡ ምን ይሰማችኋል?**

1.2.1. ሰውን የማክበር አስፈላጊነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

- **በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎች ሌሎችን ሰዎች ለምን ያከብራሉ?**

ሰውን ማክበር የኢትዮጵያውያን የጋራ ባህል ነው። አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች እርስ በእርሳቸው ይከባበራሉ፡፡ እንዲሁም አንዱ የሌላውን ክብር ይጠብቃል በመሆኑም አንዱ ሌላውን የሚያከብር ከሆነ ሌሎችም ሰዎች እሱን ያከብሩታል፡፡

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሰው ልጆች ክቡርነት ጠቀሜታዎችን ተመልከቱ፡-

• ሰብአዊ መብቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ እና ክብር ተነጥሎ የሚታይ ነገር አይደለም የሰው ልጅ ክብር ለሰብዓዊ መብት መሰረት ነው፡፡

• የሰው ልጅ ክቡርነት ለሰብአዊ እርዳታ መሰረት በመሆኑ ጓደኞቻችሁ የእናንተን እርዳታ ቢፈልጉ መርዳት አለባቹ፤ ለአብነትም በገንዘብ፣ ልብስ፣ ምግብ፣ የመጠጥ ውሃ፣ ወዘተ በመስጠት ሌሎችን መርዳት ያስፈልጋል።

• የሰው ልጅ ክቡርነት በሰብአዊ መብቶች ላይ ለሚገኙ የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ነው፤ የሰው ልጅ ሰብዓዊ መብቶች የምንላቸውን ነፃነትን እና እኩልነትን ያገኘው ሰዉ ሀኖ በመወለድ ነው፡፡

ተግባር 1.6

1. በእናንተ ማህበረሰብ ውስጥ የሰውን ክቡርነት ማክበር አስፈላጊነት ላይ ተወያዩ?
2. የክፍል ጓደኞቻችሁን ሰብዓዊ ክብር የማክበር ልምዳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ?

1.3. የሰው ልጅ መሰረታዊ ባህሪያት

1.3.1. ፍቅር

የማነቃቂያ ጥያቄ

በጣም የምትወዱት ነገር ምንድነው?

ኡፋይሴ፤ ኩማ እና ኩሲያ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ክፍል ውስጥ ሆነው ስለሚወዱት ነገር እየተከራከሩ ነበር ኡፋይሴ "አባቴን በጣም አወደዋለው ምክንያቱም ሁልጊዜ ከሥራ ሲመለስ ቸኮሌት ይዞልኝ ስለሚመጣ" ብላ ተናግራለች። ኩማ ደግሞ እናቱን በጣም እንደሚወዳት ተናግሯል። ምክንያቱ ድግሞ በሳምንት መጨረሻ ወደ መዝናኛ ቦታ ስለምትወሰደው እና እዚያም ሄዶ አሰከሚበቃው ድረስ ስለሚጫወት ነው። የኩሲያ አገላለፅ ግን ከሁለቱም የተለየ ነበር ኩሲያ እንደተናገረው ቤተሰቦቹን፤ጎረቤቶቹን፤ እና ጓደኞቹን ያለምንም ምክንያት በጣም ይወዳቸዋል። ይህንንም ሃሳባቸውን ለክፍል መምህራቸው ተራ በተራ ሲናገሩ ካዳመጣቸው በኋላ ሁሉም ልጆች ጎበዝ እንደሆኑ እና ብልህ እንደሆኑ ነግሯቸው ነገር ግን ልጆች ቤተሰባችሁን ፤ጎረቤቶቻችሁን፤ የክፍል ጓድኞቻችሁን መውደድ አለባችሁ ብለዋቸዋል። ይህንንም የምታድረጉት ቸኮሌት

ስለገዙላችሁ፤መዝናኛ ቦታ ስለወሰዱዋቹ ወይም ስለተንከባከቧችሁ ብቻ መሆን የለበትም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሰዎችን መውደድ አለባችሁ ብሎ መክሮአቸዋል፡፡

ተግባር1.7

1. ከዚህ በላይ በተገለጸው በሶስቱ ጓደኛሞች መካከል በተደረገው ውይይት የእናንተን ትኩረት የበለጠ የሳበው ማን ነው? ለምን?
2. የኩሲያ አቋም ከሌሎቹ የሚለየው ለምንድን ነው?

"ፍቅር" ማለት ጥልቅ የሆነ የወዳጅነት ስሜት እና ከሌሎች ሰዎች ወይም ነገሮች ጋር ያለንን ጥልቅ የሆን ቁርኝት ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ከአንድ ሰው ጋር ያለንን መቀራረብንና ስሜታዊ ትስስርን ማዳበር ነው፡፡ በተጨማሪም ሰዎች ከሚወዷቸው ሰዎች ሲለያዩ ልባቸው ሊሰበር እና ሊጎዱ ይችላሉ፡፡

ከታች ያሉትን ምስሎች ይመልከቱ እና ለጥያቄዎች መልስ ስጡ?



ምስል1.4ጥላቻ



ምስል1.5ፍቅር

ተግባር 1.8

1. ከላይ ካሉት ሥዕሎች ምን ተማራችሁ?
2. የእናንተ የደስታ ምንጭ ምንድን ነው?
3. ፍቅር ማለት ምን ማለት ነው?

የተለያዩ የፍቅር ዓይነቶች አሉ፡፡

1. የቤተሰብ ፍቅር፡-

የቤተሰብ ፍቅር ማለት እናትን፤ አባትን፤ ወንድምን ወይም እህትን እንደራስ አድርጎ መውደድና ለቤተሰብ ታዛዥ መሆን ማለት ነው፡፡ ቤተሰብን መውደድ በጣም ደስተኛ ያደርጋል፡፡



ምስል 1.5 ቤተሰብን መውደድ

2. የጓደኞች ፍቅር፡

ማለት በትምህርት ቤት ወይም በመንደራችን የሚገኝ ጓደኞቻንን መውደድ ማለት ነው፡፤ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲሁም በሰፈር አካባቢ ብዙ ጓደኞች አሏችሁ፤ ስለዚህ አብራችሁ ትጫወታላችሁ ፤ ትበላላችሁ፤ ትማራላችሁ እናም አብራችሁ አንዳንድ ስራዎችን ትስራላችሁ ሰለዚህ እርስ በርሳችሁ ትዋደዳላችሁ ማለት ነው፡፡



ምሰል 1.6 የጓደኛ ፍቅር

3. የሀገር ፍቅር፡-

የሀገር ፍቅር ማለት ለሀገራችን በተሰማራንበት የሥራ መስክ ጠንክረን መሥራት ማለት ነው፡፡ ሀገር ወዳድነት የጀግና ሰዎች ባህሪይ ነው። ሀገራቸውን የሚወዱ ሰዎች ለሀገራቸው በተለያየ የሥራ መስክ ሀገራቸውን ሲያገለግሉ ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ በውትድርና፤በህክምና፤ በመምህርነት፤በሩጫ እና በመሳሰሉት ሀገራቸውን ያገለግላሉ፡፡

እናንተም ሀገራችሁን የምትወዱ ሆነ በትምህርታችሁ ጠንካራ እና ጎበዝ መሆን አለባቸሁ፡፡



ምስል 1.7 የሀገር ፍቅር

ተግባር 1.9

1. እርስ በእርስ ስለመዋድድ ያላችሁ ሰሜት ምንድነው?
2. በጣም የምትወዱት ነገር ምነድን ነው?

1.3.2. ርህራሄ እና ሀዘኔታ

የማነቃቅያ ጥያቄ

ሩህሩህ እና አዛኝ ሰው መጥቀስ ትችላላችሁ?

ማዶሬ፤ አቱሞ፤ማህሌት እና ጫኬቦ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ አቱሞ የአካል ጉዳተኛ ሲሆን ባለፈው ዓመት ከትምህርት ቤት ሲመለስ ባጋጠመው የመኪና አደጋ ምክንያት አንድ እግሩን አጥቷል፡፡ ማዶሬም ከአንድ ወር በፊት እናቷን በሞት በማጣቷ በጣም ይከፋታል፡፡ በዚህም ምክንያት ትምህርት ቤት ጊቢ ውስጥ

በሚገኘው አትክልት ስፍራ ተቀምጣ ታለቅስ ነበር። ማህሌት ከክፍል ስትወጣ ማዶሬን በመጫወቻው ቦታ ባለማግኘቷ ወደ አትክልቱ ቦታ አቀናች። በዚሁ ቦታ ማዶሬ ተቀምጣ ስታለቅስ ስላገኘቻት ምን ሁነሽ ነው ጓደኛዬ ብላ ጠየቀቻት። ማዶሬም እናቷን በማጣቷ በጣም አንደሚከፋት እና መጫወት እንዳልቻለች ነገረቻት። ማህሌትም ማዶሬ አታልቅሽ ብላ ከማባበል ውጭ ምንም አላደረገችላት። በተመሣሣይ ሁኔታ ጫኬቦ ብቻውን ኩርምት ብሎ ተቀምጦ እያለ አቱሞ ደረሰ። ምን እንደሆነ ሲጠይቀዉ ምግብ እንዳልበላ ይነግረዋል፤ ምንም እንኳን አቱሞ የራሱ የአካል ጉዳት ችግር ቢኖረውም ጫኬቦን ከመርዳት አላገደውም። ትምህርት ቤት ውስጥ ወደሚገኘው የሻይ ክበብ ወስዶ ጓደኛው እንደራበውና ትምህርቱን መማር እንዳልቻለ ለመምህራኖቹ ነገራቸው። ከዚያም መምህራኖቹ ሻይ እና ዳቦ ገዝተው ጫኬቦ እንዲመገብ አድረገዋል። ስለዚህ በአቱሞ አማካኝነት የጫኬቦ ችግር ተፈቷል ማለት ነው።

ተግባር 1.10

1. ከላይ ከተጠቀሱት ተማሪዎች መካከል ማህሌትን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር? ጫኬቦንስ?

ርህራሄ እና አዘኔታ የሰው ልጅ መሰረታዊ ባህሪያት ሲሆኑ እነዚህን ፅንሰ-ሀሳቦች በተለያየ መንገድ መግለፅ እንችላለን። በሁለቱ ጽንሰ-ሃሳቦች መካከል ጥቂት ልዩነት ቢኖርም እንደየአስፈላጊነቱ እየቀያየርን እንጠቀምባቸዋለን። ሁለቱ ጽንሰ-ሃሳቦች የሚጋሯቸው የሰው ልጅ ባህሪያት ለምሳሌ እንደ ልግስና፤ ደግነት እና ራስን መውደድ ወዘተ

መግለፅ አንችላለን፡፡ ከዚህ በታች ስለ ሁለቱ ፅንሰ-ሀሳቦች በተናጠል እንወያያለን፡፡

ርህራሄ፡-

ማለት የሌሎችን ስቃይ በጥልቀት የመረዳት ችሎታ ሲሆን ያንንም ለመቀነስ የምናደርገውን ጥረትን ይጨምራል፡፡ ርህራሄ የመርዳት ፍላጎትን እንጂ ተግባራዊ የማድረግ ሁኔታን አያካትትም፡፡በሰዎች መካከል ርህራሄ ሲኖር አብሮነትን እና ወንድማማችነትን ይገነባል፡፡



ምስል 1.8 ለጓደኞችን የምናሳየው ሪህራሄ

ሀዘኔታ፡-

የሌላን ሰው ችግር እንደራስ አድርጎ የማየት እና በስቃይ ውስጥ ላሉ ሰዎች መፍትሄ የመስጠት ፍላጎትን ይገልፃል፡፡ ሀዘኔታ ለሰዎች ችግር መፍትሄ የሚያፈላልግ የሕይወት ክህሎት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ርህራሄንና ሀዘኔታን በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ሊተገብሯቸው የሚገቡ ክህሎቶች ናቸው፡፡



ምስል 1.9 ለጓደኞቻችን የምናሳየው ሀዘኔታ

ተግባር 1.11

1. **በርህራሄ እና ሀዘኔታ መካከል ያለውን ልዩነት ተወያዩ ?**
2. **ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ምስሎች ምን ትማራላችሁ?**

1.3.3 በጎ አድራጎት

የማነቃቂያ ጥያቄ

በበጎ አድራጎት ሥራ ተሰማርተው የሚገኙ ሰዎችን ወይም ድርጅት ስም ጥቀሱ?



ምስል 1.10 አበበች ጎበና ለተራቡ ሰዎች ሲመግቡ

ተግባር 1.12

1. ስለ አበበች ጎበና ምን ታውቃላችሁ?
2. ለአንድ ሰው አንድን ነገር በነጻ መስጠት ማለት ምን ማለት ነው?

በጎ አድራጎት ከፍተኛው የፍቅር አይነት ሲሆን ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ መንገድ ፍቅርን ለሌሎች ማጋራትን ያመለክታል። የበጎ አድራጎት ተቋም ማለት ገንዘብ በማሰባሰብ የሌሎች አካላት እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ማለትም የታመሙ፣ ችግረኞችንና የአካል ጉዳት ያለባቸውን የሚረዳ እና ለማህበረሰብ ጥቅም የሚሰራ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው። በመሆኑም እርዳታ የሚፈልጉ ተጎጂዎች

በጦርነት የተፈናቀሉ ፣ የተፈጥሮ አደጋዎች ማለትም ረሃብ፣ በሽታ፣ ድህነት እና ወላጅ አልባ ህጻናትን የሚረዳ ድርጅት ነው።፤ በሌላ አነጋገር ሰዎችን ያለምንም ክፍያ በነጻ የሚረዳ ተቋም ነው።።

ተግባር 1.13

1. ስለ በጎ አድራጎት ምን ታስባላችሁ?
2. በዙሪያችሁ ላሉ ችግረኞች የእናንተ አስተዋፅዖ ምንድን ነው?

1.3.4 በጎ ፍቃደኝነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

- በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎች የሚያከናውኗቸው የበጎ ፍቃደኝነት ስራዎችን መጥቀስ ትችላላችሁ?
- ከታች ያለውን ምስል ይመልከቱ እና ተማሪዎቹ ምን እየሰሩ እንደሆነ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?



ምስል 1.11ተማሪዎች በበጎፍቃድኝነት ሲሳተፉ

ተግባር 1.14

1. በምስሉ ላይ ስላሉት ተማሪዎች ድርጊት ምን ይሰማችኋል?

2. በትምህርት ቤታችሁም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ በእንደዚህ አይነት ድርጊቶች ላይ በፈቃደኝነት ተሳትፋችሁ ታውቃላችሁ?

በጎ ፈቃደኝነት ጊዜአችንን እና ያለንን ችሎታ ለሌሎች ጥቅም የማዋል ልምድ ነው፡፡ በጎ ፍቃደኞች በነፃ ጊዜያቸውን እና ጉልበታቸውን ለማህበረሰብ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ሁሉንም ሥራ የሚያከናውኑት ለገንዘብ ጥቅም ሳይሆን ለመንፈስ እርካታ እና ህበረተሰቡን ለመጥቀም ነው፡፡ በጎ ፍቃደኞች በተለያዩ ተግባራት ይሳተፋሉ፡- ለምሳሌ በአካባቢ ጥበቃ ስለ አካባቢ ጥበቃ በማስተማር ፤ እንድሁም በድንገተኛ አደጋ የተጎዱ ሰዎችን መርዳት እና በደም ልገሳ ይሳተፋሉ ፡፡

ተግባር 1.15

ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ውስጥ በበጎ ፍቃደኝነት እንድትሳተፉ ያበረታታችኋል

3.3.5. ትህትና

የማነቃቂያ ጥያቄ

ከሰዎች ጋር ስትገናኙ በምን አይነት መልኩ ትህትናቸሁን ታሳያላችሁ?



ምስል 1.12 ትህትና

ተግባር 1.16

1. **ከላይ ካለው ምስል ምን ትማራላቹ ?**

"ትህትና " ለሌሎች አክብሮት ማሳየት ሲሆን የሌሎችን ማንነት፣ ፍላጎት እና እምነት ሳያጓድሉ ጨዋነት በተሞላው መልኩ ለሌሎች ፍቅርን እና መልካም ግብረ ገብነትን የማሳየት ዝንባሌ ነው ። በተጨማሪም ትህትና

ከሌሎች ጋር ያላችሁን ጥሩ ግንኙነት፤ መከባበር ፤ራስን መቆጣጠር፤ እንግዳ ከሆኑ ሰዎች ጋር መልካምነት መፍጠርን ያጠቃልላል፡፡

ትህትና ብንላበስ የሚከተሉትን ጥቅሞች እናገኛለን ፡፡

የሌሎችን መብት እንድናከብር ያስችለናል፤

- የሌሎችን ክብር እንድናዉቅና እንድንጠብቅ ያስችለናል፤
- በሰዎች ሁሉ የተፈጥሮ መልካምነት እንድናምን ያስችለናል፤

ጥሩ ምሳሌ

በተለያዩ ቦታዎች ትህትናችንን ማሳየት ይኖርብናል ። ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች እግር ኳስን ይጫወታሉ፡፡ ከተጫዋቾቹ አንዱ ቢጎዳ ወይም ቢቆስል ሌላኛው ሊረዳው ይገባል፡፡ ይህ አንደኛው ትህትናን የምናሳይበት መንገድ ነው።



ምስል 1.13 ትህትና በኳስ ሜዳ ውስጥ

ተግባር 1.17

1. ከላይ ካለው ሥዕል ምን ተማራችሁ?

2. ጨዋነት ምንድነው? ስለ ጨዋነትየምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ?

1.3.6 ወንድማማችነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

- በጣም የምትወዱትን የትምህርት ቤት ጓደኛችሁን ወይም ጎረቤቶቻችሁን ማን ብላችሁ ትጠራላችሁ? መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ

ወንድማማችነት በጓደኝነት ወይም በሰዎች መካከል ያለ የወዳጅነት ስሜት ሆኖ በሰዎች መካከል ያለ ወንድማማችነትን ወይም እህትማማችነትን ያሳድጋል። በተጨማሪም በቡድን ውስጥ ያሉ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ተመሳሳይ አላማ እንዲኖራቸው ያደርጋል። በመሆኑም በተመሳሳይ መስሪያ ቤት የሚሰሩ ሰዎች ተመሳሳይ አላማና ግብ አላቸው። በተመሳሳይ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎችም ተመሳሳይ አላማ አላቸው ማለት ነው።



ምስል 1.14 ወንድማማችነት ወይም እህትማማችነት

ተግባር 1.18

1. ከላይ ካለው ምስል ምን ተማራችሁ?
2. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ እንደ እህትና ወንድም ያለ ቡድን አለ?
3. የወንድማማችነትን አስፈላጊነት ግለጹ?

ከላይ ከተጠቀሰው የወንድማማችነት ትርጉም በመነሳት በተመሳሳይ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች የወንድማማችነት ስሜትን ማዳበር ይችላሉ፡፡ ስለዚህም በወንድማማችነት መንፈስ ጓደኝነታቸውን ማጠናከር እና አንዱ ሌላውን እንደ ወንድም ወይም እህት መመልከት ይኖርበታል፡፡ በተማሪዎች መካከል የወንድማማችነት ስሜትን ስታሳድጉ የወደፊት ግንኙነታችሁን ጠንካራ ታደርጋላችሁ፡፡

1.3.7. ትዕግስት

የማነቃቂያ ጥያቄ

መምህራችሁ ወደ ክፍል እሰኪገቡ ድረስ ምን እያደረጋችሁ ትጠብቃላቸሁ?

ውይይት

ብሌን፡-ቤተሰቦችህ እገዛልሃለው ያሉትን ነገር ሳይገዙ ቢዘገዩ ምን ይሰማሃል?

ዛዳላ፡- የገቡልኝን ቃል እስኪፈፅሙለኝ ድረስ በየምሽቱ እረብሻቸዋለሁ።

ብሌን፡- እንዴ ይህ መጥፎ ባህሪ ነው፤ ታጋሽ መሆን አለብህ።

ዛዳላ፡ እባክሽ ታጋሽ መሆን ስትይ ምን ማለትሽ ነው?

ብሌን፡- ታጋሽ ማለት ሳይረብሹ በተረጋጋ ሁኔታ የፈለከውን ነገር መጠበቅ ነው። እኔ ሁልጊዜ የማደርገው ይህንን ነው።

ዛዳላ፡ አመሰግናለሁ ብሌን! ያልሽኝን ተግባራዊ አደርጋለሁ።

ተግባር 1.19

1. **ብሌን እና ዛዳላ ካደረጉት ውይይት ምን ተማራችሁ?**
2. **ስለ ትዕግሰት ያላቸሁን ልምድ ለቡድን አባላት አካፍሉ።**



ምስል1.15. በክፍል ውስጥ ተማሪዎች መምህራቸውን በትግስት ሲጠብቁ

ለምሳሌ መምመህራችሁ ወደ ክፍል ዘግይቶ ቢመጣ በትዕግሰት መጠበቅ ይኖርባቸኋል፡፡ እንደዛውም ቤተሰቦቻችን ልብስ እገዛለው ብለው ሳይገዙ ቢዘገዩ ለምን አልገዙልኝም ብለን ከማኩረፍ ወይም ከመረበሽ ይልቅ የነሱን ችግር መረዳት እና እነሱ አስበው አስክያደርጉልን ድረስ በትዕግስት መጠበቅ ይኖርብናል፡፡

ትዕግስት ማለት ነገሮችን በታጋሽነት የመጠበቅ እና የማከናወን ብቃት ነው፡፡ ትዕግስት የሚለው ፅንሰ ሐሳብ ፈተናዎችን እና ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ በመቀበል እና በመታገስ ለመፍታት መሞከር ማለት ነው፡፡ ታጋሽነት በሰላም ለመኖር ቁልፍ ተግባር ነው፡፡

13.8 ሰላም

የማነቃቂያ ጥያቄ

የምታውቋቸውን ሰዎች ስታገኙ እንዴት ሰላም ትላላችሁ?

ሰላም ማለት ያለምንም ጥላቻና ጥቃት የህብረተሰብ ወዳጅነት እና ስምምነት ማለት ነው። በተጨማሪም አካባቢያችን ከመጥፎ ነገሮች የፀዳ ማለትም ከጦርነት፤ ከአለመረጋጋት፤ከጥቃት፣ እና ከኢ-ፍትሃዊነት የጸዳ ከሆነ ይህንን ሰላም ልንል እንችላለን።

ሰዎች ምቹ ባልሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳን ሰላምታ ይለዋወጣሉ ። እንዲሁም ከሰዎች ጋር ስንገናኝ ሲገናኙ ሰላም ይባባላሉ ። በመሆኑም ሰላምታ የመልካም ግንኙነቶች መገለጫ ነው። ሰላምታ ለሰላም ከፍተኛ አስተዋጸኦ አለው በተጨማሪም የጥሩ ግኑኝነት ማሳያም ነው ። ሰላም ሲኖር ሰዎች ሀሳባቸውን ይገልፃሉ ይጫወታሉ ይግባባሉ፤ ይከራከራሉ ወዘተ ሁሉንም ማድረግ ይችላሉ ። ሰላም በተማሪዎች መካከል የወንድማማችነትን የመተባበርን ስሜት ይፈጥራል። ስለዚህ ሰላም አብሮ ለመኖር ወሳኝ ከመሆኑም ባሻገር በቤተሰብ፤ በጎረቤት፤ በሀገር መካከል ላለ ፍቅር መሠረት ነው።

ተግባር 1.20

1. **በኮቪድ 19 ወቅት ለሰዎች ሰላምታ የምትሰጡበትን መንገድ አሳዩ?**
2. **በሰላም እና ሰላምታ መካከል ያለውን ግንኙነት ተወያዩ?**

ስለ ሰላም አለመኖር የሚከተሉትን ስዕሎች ይመልከቱ



ምሰል1.17. በጓደኞች መካከል ግጭት

ተግባር 1.21

1. ከላይ ካለት ሥዕሎች ምን ተማራችሁ?

2. እርስ በእርስ መጣላት የሚያመጣውን መጥፎ ጎን ለክፍል ጓደችሁ ንገሩ?

ሰላም ማጣት ወደ ግጭት ያመራል። ግጭት መጥፎ ተግባር በመሆኑ እርስ በእርስ ወደ መጣላት ያመራል። ከጓደኛችሁ ጋር ከተጣላችሁ አንዱ ሌላውን ሊጎዳው ይችላል። ሁለታችሁም ተጎጂ ልትሆኑ ትችላላችሁ። በዚህም ተግባር ጥርሳችሁን፣አይናችሁን ወይም ሌላ የሰውነት ክፍላችሁን ልታጡ ትችላላችሁ።

የምዕራፍ ማጠቃለያ

ሰብአዊነት የሰውን ተፈጥሮ እና የሰውን ቅንነት /ደግነት/ ያመለክታል። ሰብአዊነት የሁሉንም ሰዎች እኩልነት ያለምንም አድሎ እና መገለል የሚያረጋግጥ ነው። ሁላችንም ለሰብዓዊነት ቅደሚያ በመስጠት ማክበር ይጠበቅብናል። ሰብአዊነትን ማክበር ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ተለይቶ የሚታይ ነገር አይደለም ። የሰው ልጅ ክብር የሚለው ፅንሰ-ሀሳብ ሰው ከመሆን ተለይቶ የማይታይ እና ለሰው ልጅ ከሚሰጥ ዋጋ እና ግምት የተቆራኘ ነው ። እንደየግለሰቡ ባሕርይ እና ተግባር አንፃር ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን ሊነፈጉ ይችላሉ።ሰብዓዊነትን ማክበር እና መንከባከብ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። በተለይም ለሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ፣ ሰብዓዊ እርዳታን ተደራሽ ለማድረግ እና የሰብአዊ መብት ህጎች ተግባራዊ ለማድረግ የሰውን ልጅ ማክበር ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ሰብአዊነት መሰረታዊ ባህሪያት ያሉት ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፤ ፍቅር፣ ርህራሄ፣ በጎነት፣ በጎ ፈቃደኝነት፣ ጨዋነት፣ ወንድማማችነት፣ ትዕግስት፣ ሰላም፣ መከባበር እና ፍትሃዊነት ናቸው።

ቁልፍ ቃላት

ደግነት፡- መልካም ሆኖ መገኘት

ክብር፡- ሌሎችን ማክበር ወይም የራስን ክብር መጠበቅ

ርህራሄ:- የአንድን ሰው ስሜት የመጋራት ችሎታ፡

ፍርድ:- ጥሩ ውሳኔዎችን የመወሰን ችሎታ

የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ መልመጃ ጥያቄዎች

<u>ክፍል አንድ፡</u> አ.ርፍት ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህትት ከሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. ሰብአዊነት የሁሉንም ሰዎች እኩልነት ያረጋግጣል፡፡

2. የሰውን ሰብአዊ ክብር ማስጠበቅ የአንዳንድ ሰዎች ኃላፊነት ብቻ ነው።

3. ትዕግስት ነገሮችን ሳያጉረመርሙ በረጋ ሁኔታ የማከናወን ችሎታ ነው።

4. "ሥነ-ምግባር" ለሌሎች ትህትናን ማሳየት ነው፡፡

5. በጎ ፈቃደኝነት ለራስ ጥቅም ጊዜን እና ክህሎቶችን የመስጠት ልምምድ ነው፡፡

<u>ክፍል ሁለት፡</u> ፅንሰ-ሀሳቦችን ከሚመለከታቸዉ ማብራሪያዎች ጋር አዛምዱ፡፡

አመድ ሀ	አምድ ለ
1. ጥልቅ የሆነ የወዳጅነት ስሜት	ሀ. ርህራሄ
2. ከፍተኛው የፍቅር ዓይነት	ለ. ፍቅር
3. ለሌሎች አክብሮት ማሳየት	ሐ. የበጎ አድራጎት ድርጅት
4. ለሌላ ሰው ዋጋ የመስጠት እና የማክበር ችሎታ	መ. ስልጣኔ
5. የሌሎችን ስቃይ መረዳት	ሠ. አክብሮት

<u>ክፍል ሶስት፡</u> ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ሰብዓዊነትን የማክበር አስፈላጊት የማይገልፀው የትኛው ነው?

   ሀ. ለሰብአዊ መብቶች መሰረት ነው፤

   ለ. ለሰብአዊ እርዳታ መሰረት ነው፤

   ሐ. ለሰብአዊ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፤

   መ. ለሰብአዊ መብት ጥሰት መሰረት ነው፤

2. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ግለሰቦች በነጻነት የሚሳተፉበት እና ምንም አይነት ክፍያ ሳይኖራቸው አገልግሎት የሚሰጡት ተግባር የትኛው ነው?

   ሀ. ጨዋነት

   ለ. ወንድማማችነት

   ሐ. በጎ ፈቃደኝነት

   መ. ትዕግስት

3. ከሚከተሉት ውስጥ ተቀባይነት ባላቸው ደረጃዎች ላይ የተመሠረተ የሰዎችን ፍትሃዊ እና ምክንያታዊ አያያዝን የሚያመለክተው የቱ ነው?

   ሀ. ሰላም

   ለ. ፍትሃዊነት

   ሐ. ርኅራኄ

   መ. በጎ አድራጎት ድርጅት

ክፍል አራት፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ ሥሩ

1. **የሰውን ክብር የመጠበቅ አስፈላጊነትን ዘርዝሩ።**
2. **ሰዎች በማህበረሰብ ውስጥ የራሳቸውን ክብር በምን ምክንያት ሊያጡ እንደሚችሉ በዝርዝር አስቀምጡ ።**
3. **በቤት ውስጥ ወላጆቻችሁን እንዴት እንደምታከብሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?**
4. **በትምህርት ቤት እና በአከባቢያችሁ በበጎ ፈቃደኝነት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ትሳተፋላችሁ? ከተሳተፋችሁ በምን በምን? ጥቂት ምሳሌዎችን ስጡ?**

ምዕራፍ ሁለት

ሌሎችን ማክበር

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፡-

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ።

- **ሌሎችን የማክበር ጽንሰ-ሀሳብን ታብራራላችሁ፣**
- **ለሌሎች ክብር የመስጠትን አስፈላጊነት መግለጽ ትችላላችሁ፤**
- **የሌሎችን አመለካከት እና ፍላጎት ማድነቅ ትችላላችሁ፤**
- **የተከበሩ ሰዎችን ባህሪያት ታሳያላችሁ፤**
- **ሌሎችን አለማክበር የሚያስከትለውን ውጤት ትለያላችሁ፤**

መግቢያ

ይህ ክፍል ሌሎችን ስለማክበር የሚያብራራ ምዕራፍ ነው። ሌሎችን ሰዎች የማክበር ጥቅም እና አስፈላጊነት በሚለው ላይ ሀሳብ ይቀርባል። ይህንንም ስንል በማህበረሰባችን ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች፤ ማለትም በእድሜ የገፉ ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ መምህራን፣ ቤተሰብ፣ ጎረቤቶቻችን፣ እና የክፍል ጓደኞቻችንን የማክበር አስፈላጊነትን ያብራራል። በተጨማሪም ምዕራፉ የተከበሩ ሰዎች ባህሪያትን እና ሰውን አለማክበር የሚያመጣውን መዘዝ እና ጉዳት ይዘረዝራል።

2.1. አክብሮት

የማነቃቂያ ጥያቄ

1. ሌሎችን ሰዎች ስለማክበር የምታስቡትን ለክፊል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ?
2. ለሰዎች ያላችሁን ክብር በምን አይነት መልኩ ማሳየት ትችላላችሁ?



ምስል 2.1 ሌሎችን ማክበር

አክብሮት ለሌላ ሰው ዋጋ የመስጠት እና የማክበር ችሎታን ያሳያል። አክብሮት በሁለት መንገድ ሊገለፅ ይችላል በድርጊቶች ወይም በቃላት። የሰው ልጅ በየትኛውም ቦታ መከበር አለበት። መከባበር ሰዎች እርስ በእርስ የመተማመን ስሜት እንድያዳብሩ እና እንድያሳድጉ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት

ያጠናክራል፡፡ አንዱ ሌላውን ማክበር በመማር ወይም በልምምድ የሚመጣ እንጅ አብሮ የሚወለድ አይደለም፡፡ ሦስት የአክብሮት አይነቶች አሉ እነሱም፡-

ሀ. ራስን ማክበር፤
ለ. ለሌሎች አክብሮት መስጠት፣ እና
ሐ. ሌሎች ሰዎች ለእኛ ያላቸው አክብሮት ናቸው፡፡
የመከባበር መርህ እንደሚለው ከሆነ አንድ ሰው የመከበር ፍላጎት ካለው መጀመሪያ ሌሎች ሰዎች ማክበር አለበት።

ተግባር 2፤

1. በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ አንዱ ሌላውን የሚያከበርበትን መንገዶች አሳዩ?
2. ስለ አክብሮት ያላችሁን መረዳት ለቡድኖቻችሁ እና ለመምህራችሁ አብራሩ?

2.2. ሌሎችን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ፤

ከሰዎች ጋር ስትገናኙ ምን ታደርጋላችሁ?
ከላይ እንደተማርነው አክብሮት ለራሳችን እና ለሌሎች ያለንን የማክበር ፍላጎት የምናይሳበት መንገድ ነው፡፡ “ሌላ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከራሳችን በስተቀር ያለን ማንንም ሰው ማለት ነው።

ነገር ግን በዚህ ክፍል ውስጥ የምናተኩረው በአንዳንነድ ማህበራዊ ቡድኖች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

ሌሎችን ማክበር የሚጀምረው ሰዎች በራስ የመወሰን ብቃታቸው፣ የተለዩ እና ነፃ ስለመሆናቸው እውቅና ስንሰጥ ነው፡፡ ሌሎችን ስናከብር ሰብዓዊ ክብራቸውን እናረጋግጣለን እንዲሁም ለሰዎች ሰብዕና ዋጋ መስጠትንና ማክበርን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ማህበራዊ ደረጃዎች የሚገኙ ሌሎች ሰዎችን ማድነቅና እውቅና መስጠት ሌሎችን ከማክበር ጋር ይያያዛል፡፡



ምስል 1.2፡ እርስ በእርስ መከባበር

ከላይ በሥዕሎቹ ላይ እንደተመለከታችሁት ለሌሎች ያለንን ክብር በተለያየ መንገድ መግለጽ እንችላለን፡፡ የሚከተሉትን ድርጊቶች በመጠቀም እኛ ለሌሎች ያለንን አክብሮት ማሳየት እንችላለን ይኸውም ሰላምታ፣ ጨዋነት፣ ደግነት፣ ምስጋና እና መታዘዝ ናቸው፡፡

ተግባር-3

1. በየቀኑ የምትለማመዱት ከላይ ከተጠቀሱት ድርጊቶች መካከል የትኛውን ነው?

2.በየቀኑ የምታደርጉትን ልምድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ?

3. ለሌሎች ሰዎች አክብሮት ስታሳዩዋቸው ምን ይሰማቸዋል?

2.3. ሌሎችን የማክበርን አስፈላጊነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

- ሌሎች ሰዎችን የማክበር አስፈላጊነትን በአጭሩ ግለፁ?

ሌሎች ሰዎችን ማክበር ክብር የሚሰጠውንም ክብር የሚቀበለውንም ይጠቅማል፡፡ በጓደኝነት፣ በግለሰባዊ ግኑኝነት ውስጥ መከባበር ትልቅ ቦታ አለው፡፡ይኸውም ደህንነት እንዲሰማን እና ደስተኛ እንድንሆን ይረዳናል፡፡ ምክንያቱም ሌሎችን ስናከብር ሌሎች እኛን በክብር እና በመልካም ሁኔታ እንዲያዩን ይረዳል፡፡ በሌሎች የመከበር ስሜት የሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ አንደዚሁ ሌሎችን ማክበር መልካም ግኑኝነቶችን፣ ሰላምን፣ እና እርስ በእርስ የመተባበር ስሜትን በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲስፋፉ ይረዳል፡፡

ተግባር- 2.4

1. በማነቃቂያ ጥያቄ የተሰጠውን መልስ ከራሳችሁ መልስ ጋር አነፃፅሩ?
2. ሌሎችን ማክበር ለእናንተ የሚያበረክተውን አስተዋጽያ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ?

የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን የማክበር አስፈላጊነት

2.3.1. የእድሜ ባለፀጋዎችን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

- በአካባቢያችሁ ያሉትን የእድሜ ባለፀጋዎች ሥም መጥቀስ ትችላላችሁ?

የእድሜ ባለፀጋ ማለት ከእናንተ በዕድሜ የሚበልጥ ማንኛውም ሰው ሲሆን እነሱም እናንተን በዕድሜ የሚበለጡ ወንድሞች፣ እህቶች፣ የክፍል ጓደኞች እና ጎረቤቶችን ያካትታል። በእድሜ የገፉ ሰዎች በተለምዶ "አዛዉንቶች" ይባላሉ።ለምሳሌ እናቶች፣ አባቶች፣ወንድ አያቶች፣ሴት አያቶች፣ ወዘተ ናቸው። ሰዎች በዕድሜያቸው ሳይሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ቦታ፣ አስተዋፅኦ እና በማህበራዊ ተቀባይነት ምክንያት ሽማግሌ ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ።።ለዚህም እንደ ምሳሌ የማህበረሰብ መሪዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ እና የተከበሩ ሰዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ።።

ተግባር 2.5

1. ከላይ ከተዘረዘሩት አዛዉንቶች መካከል ምን ያህሉን እንደምታውቋቸው መጥቀስ ትችላለችሁ?

2. የምታውቋቸውን አዛውንቶች በክፍል ውስጥ ስታገኟቸው ምን ምላሽ እንደምትሰጡ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ?

አረጋውያንን፣ የማህበረሰቡ መሪዎችን፣ እና የሀይማኖት ተቋማት መሪዎችን ለማክበር ጨዋ መሆንን ይጠይቃል። ይህ ለእድሜ ባለፀጋ ያለንን ቦታ ያሳያል። ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ቦታ የሚገኝ የጋራ እና ተመሳሳይ የሆነ የሥነ ምግባር መርህ አለ ይህም ትልልቅ ሰዎችን ማድመጥ የሚል ነው። በመሆኑም ሁልጊዜ የእድሜ ባለፀጋዎችን ማድመጥና እንድንፈጽም የሚያዙንን ተግባራዊ ማድረግ አለብን ማለት ነው። የእድሜ ባለፀጋዎችን ማክበር ማለት፡-

- ስናገኛቸው በትህትና ማናገርና የሚነግሩንን ምክር በጥንቃቄ ማድመጥ፣
- ለሚጠይቁን ጥያቄዎች በአክብሮት እና በትህትና ምላሽ መስጠት፣
- ሲናገሩ አለማቋረጥ ጥያቄ እና ድጋፍ ካለን እንኳን ሀሳባቸውን ተናግረው አሰኪጨርሱ መጠበቅ፣
- ማድነቅ እና ማክበር።



ምስል 2.3፡- ለትልልቅ ሰዎች ቅድሚያ መስጠት

ተግባር-2.6

1. ከላይ ካለው ሥዕል ምን ተማራችሁ?
2. ይህንን በማድረጋችሁ ደስተኛ ናችሁ?
3. ትልልቅ ሰዎችን ማድመጥ በሚለው መርህ ውስጥ በእናንተ አካባቢ ያለ ተመሳሳይ ልምድ ካለ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ?

2.3.2 የሀይማኖት አባቶችን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

የሃይማኖት አባቶችህን ስም ለክፍል ጓደኞችህ ንገራቸው?

የሃይማኖት አባቶች ማለት በእምነት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ መሪዎች ማለት ነው፡፡ የሃይማኖት አባቶች በእምነት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ እነዚህም የሃይማኖት ተቋም መሪዎች ልንላቸው እንችላለን፡፡ የሃይማኖት መሪዎች ማዕረግ እና ተግባራቸው እንደየ ሃይማኖታቸው

የተለያየ ነው፡፡ ጳጳሳት፣ ቄሶች፣ ኢማሞች፣ እና ፓስተሮች ናቸው፡፡ የሃይማኖት አባቶች በማህበረሰቡ ውሰጥ በጣም የተከበሩ እና ለማህበረሰቡ አርአያ የሚሆኑ ናቸው፡፡



ምስል-2.4 የሀይማኖት አባቶችን ማክበር

የሃይማኖት አባቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በርካታ ተግባራት አሏቸው ከነዚህም ውስጥ፡

- ሰዎች ጥሩ ስነ-ምግባር እንዲኖራቸው ማስተማር እና መምከር፣
- ግጭት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ማስታረቅ፣
- የግለሰቦችን ባህሪይ ተቀባይነት ባለው መንገድ መቅረጽ ወዘተ ናቸው፡፡

ስለዚህ የሃይማኖት አባቶችን ማክበር ማለት፡-

• በሃይማኖቱ ተከታይ ውስጥ ያላቸውን የላቀ ክብር ግምት ውስጥ ማስገባት፣

• ምክራቸውን እንደግለሰብም ሆነ እንደማህበረሰብ መቀበል፣

• ያዘዙትን ለማዳመጥ እና ለመተግበር ፈቃደኛ መሆን፣

• በምክራቸው መሰረት መስራት፣ ወዘተ ማለት ነው።።

ተግባር 2.7

1. የሃይማኖት አባቶቻችሁን ታከብራላችሁ?
2. የሀይማኖት አባቶችን ስለማክበር አስፈላጊነት ተወያዩ?

2.3.2 *መምህራንን ማክበር*

የማነቃቂያ ጥያቄ

በክፍል ውስጥ ያለውን የመምህራችሁን ስም ተናገሩ።።



ምስል 2.5፡- መምህርን በ ክፍል ውስጥ ማክበር

ተግባር 2.8

1. ከላይ ካለው ምስል ምን ተማራችሁ?

2. ከላይ ያለው ምስል እና እናንተ በክፈል ውስጥ ከምታደርጉት ጋር ሲወዳደር ምን ልዩነት አለ?

3. መምህራችሁን ስታከብሩ የሚሰማችሁን ስሜት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ?

መምህር ማለት ተማሪዎችን በትምህርት ቤት የሚያስተምር ወይም የሚመራ ማለት ነው። መምህራን የተማሪዎችን ባህሪ መቅረጽ እና ልጆች በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያለው ባህሪ አንዲኖራቸው የማድረግ ትልቅ ሀላፊነት አለባቸው።

ሰለሆነም ተማሪዎችም ሆኑ የተማሪ ወላጆች መምህራኖችን ማክበር እና ለተማሪዎች የሚሰጡትን ምክርም ሆነ ተግሳፅ መቀበል እና ለመተግበር ዝግጁ መሆን አለባቸው። ይህን ማድረግ ከመምህራን ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖር ይረዳችኋል። ይህ መልካም ግንኙነት በተማሪዎች ውጤት እና ባህሪ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል።

ስለዚህ ለመምህራኖቻችን በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥም ሆነ ውጭ ትሁት እና ታዛዥ መሆን አለብን። መምህራኖች ደግሞ የተማሪዎቻቸውን ባህሪ መቅረፅ ተማሪዎችን መውደድ እና ክብራቸውን መጠበቅ አለባቸው።

2.3.4. ቤተሰብን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

*** የቤተሰቦቻችሁን ስም ዘርዝሩ?**

ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ውስጥ በጋራ የሚኖሩ የሰዎች ስብስብ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ቤተሰብ በዝምድናም ሊገለጽ ይችላል፡፡ ይህ ማለት የሰዎች ስብስብ ሆኖ ተመሳሳይ አያቶች ወይም ቅድመ አያቶችን የሚጋሩ ከሆነ አነዚህንም ቤተሰብ ብለን ልንጠራ እንችላለን፡፡ እንደ አንድ የማህበረሰብ ክፍል ቤተሰብ የሚያጠቃልለው ወላጆችን እና ልጆችን ሲሆን የቤተሰብ አባላት ብለን የምንጠራቸው በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ እናት፤ አባት፤ እህት፤ ወንድምና ሌሎች ናቸው፡፡

የቤተሰብ አባላትን ማክበር ሚጀምረው ለቤተሰቦቻችን ያለንን ጥልቅ ፍቅር እና አድናቆት በማሳየት ነው፡፡ሰለሆነም ቤተሰብን መውድድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም በቤተሰብ ውሰጥ ፍቅር እና መልካም ግንኙነት ከሌለ ደስተኛ ቤተሰብ ሊኖር አይችልም፡፡ ፍቅር እና መከባበር ለአንድ ቤተሰብ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡ ለቤተሰቦቻችን ፍቅራችንን የምንገልፅባቸው መንገዶች የተለያዩ ናቸው ለምሳሌ ትሁት መሆን፣ መታዝዝ፣ ቤተሰቦቻችን የሚሉንን ማዳመጥ፣ እና የእነሱን ውሳኔ መቀበል ከእኛ የሚጠበቁ ተግባራት ናቸው ፡፡



ምስል 2.6፡- ቤተሰብን መርዳት

ተግባር- 2.9

1. ቤተሰቦቻችሁን ታከብራላችሁ?
2. ቤተሰቦቻችሁን እንዴት አድርጋችሁ እንደምታከብሩ ያላችሁን ተሞክሮ ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ?
3. ቤተሰብን የማክበርን አስፈላጊነት ተናገሩ?

2.3.5. ጎረቤቶችን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

በቤታችሁ አቅራቢያ የሚኖሩ ቢያንስ የአምስት ሰዎችን ስም መጥቀስ ትችላላችሁ?

ጎረቤቶች ማለት ከእኛ ጋር አብረው በቅርበት የሚኖሩ ሰዎች ሲሆኑ በመኖሪያ ቤት፣ በአፓርታማ፣ ኮንዶሚኒየም እና በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን ጎረቤቶች ልንላችው አንችላለን ፡፡

መልካም ጎረቤቶች የምንላቸው ቤተሰብ ችግር በሚያጋጥመው ጊዜ እርዳታ የሚሰጡ እና አደጋ ሲከሰት ከቤተሰብ ጎን የሚቆሙ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በሀዘንም ሆነ በደስታ ግዜ ከጎናችን የሚሆኑ ማለት ነው፡፡

ሰላማዊ የሆነ ሕይወት ለመኖር ጎረቤቶችን ማክበር እንደ ቅድመ-ሁኔታ ሊቀመጥ የሚገባው ነገር ነው፡፡ ከጎረቤት ጋር መልካም ግኑኝነት መፍጠር ለትብብር ዋናው መሰረት ነው፡፡ በጎረቤት መካከል የሚኖረው መቀራረብ መልካም የሆነ ግንኙነት እንዲፈጠር ያግዛል፡፡ የመልካም ጉርብትና መኖር በሀበረተሰብም ሆነ በሀገር ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ ያግዛል፡፤



ምስል 2.7 ፡- ጎረቤቶቻችንን ማክበር

ለጎረቤቶቻችን አክብሮት የምናሳይባቸው መንገዶች፡-

• ለጎረቤቶቻችን ሰላምታ መስጠት ፣ከእነሱ ጋር መገናኘት እና ስማቸውን ማወቅ ፣

• በአካባቢያችሁ በተለያዩ ሥራዎች መሳተፍ፣

• በማህበረሰብ ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ፣

• የአካባቢያችሁን ንጽሕና መጠበቅ፤

• ጎርቤቶቻችሁን አለመረበሽ፤

ተግባር 2.10

1. ለጎረቤቶቻችሁ አክብሮት የምታሳዩባቸውን መንገዶች ጥቀሱ?
2. በክፍል ውስጥ ጎረቤታችሁን እንዴት እንደምታከብሩ አሳዩ?
3. ጎረቤትን የማክበር አስፈላጊነትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?

2.3.6. የክፍል ጓደኞችን ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄ

• ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስፈላጊውን ሰላምታ ወይም ክብር ትሰጣላቸሁ? በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ሁሉም ተማሪዎች የክፍል ጓደኞቻችሁ ናቸው። በሌላ አነጋገር፣ በትምህርት ቤት ውስጥ በተመሳሳይ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎችን የክፍል ጓደኞች ልንል አንችላለን፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ጓደኞች በጣም ጥሩ ጓደኞች ናቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ የክፍል ጓደኞች አብረው የሚማሩ ሲሆኑ ከተለያዩ ቤተሰብ የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንዱ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ካላቸዉ ቤተሰብ የመጡ አንዳንዱ ደግሞ ከሃብታም ቤተሰብ የመጡ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም የክፍል ጓደኞች የተለያዩ ናቸው፤ ለምሳሌ በቆዳ ቀለም፣

በሃይማኖታዊ ዳራዎች፣ እና በቋንቋ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክፍል ውስጥ ያለው ልዩነት በትምህርት አቀባበል ላይ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንዶች በጣም ጎበዝ አንዳንዶች መካከለኛ ወይም ዝቅተኛ አቀባበል ሊኖራቸው ይችላል፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ቢኖሩም እንኳን ሁሉም የሰው ልጆች ናቸው፤ ሁላችሁም የምትማሩት ተመሳሳይ በሆነ ክፍል ውሥጥ ነው ፡፡ስለዚህ ጓደኛሞች ናችሁ ማለት ነው፡፡



ምስል2.8. የክፍል ጓደኞቻችንን የምናከብርበት መንገድ

የክፍል ጓደኞችን ማክበር ልዩነታቸውን መቀበል እና ከእነርሱ ጋር አዎንታዊ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ጥሩ ግንኙነት ጥሩ ጓደኝነትን ይመሰርታል ፡፡ ጓደኝነት መመስረት አብራችሁ እንድትጫወቱ ፣በትብብር እንድትማሩ እና አብራችሁ እንድትበሉና እንድትጠጡ ያስችላችኃል፡፡ ይህ ደግሞ በክፍል ውስጥ እና ከክፍል

ውጭ ብልህ እና ንቁ ተማሪ እንድትሆኑ ያግዛችኃል። የክፍል ጓደኞቻችንን የምናከብርበት መንገድ የሚከተሉት ናቸው

• ሲገናኙ ሞቅ ያለ ሰላምታ መስጠት

• ከአንድ ሰው ጋር በሚገናኙበት ጊዜ በጥሞና እና በታማኝነት ማዳመጥ።

• ችላ አለማለት

• ቅንነት ማሳየት እና አድናቆትን መግለጽ ፣

• ደህንነታቸውን እና ስሜታቸውን መጠበቅ።

ተግባር 2.11

1. ጓደኞቻችሁን ምን ያህል እንደምታከብሯቸዉ ንገሯቸዉ?
2. እርስ በእርሳችሁ የምትከባበሩበትን መንገዶች በክፍል ውስጥ አሳዩ?
3. አንዳችሁ ለሌላኛዉ ያላችሁን አክብሮት ግለጹ?

2.4. የተከበሩ ሰዎች ባህሪያት

የማነቃቂያ ጥያቄ

የተከበሩ ጓደኞችህን ባህሪያት ዘርዝር?

የተከበሩ ሰዎች የራሳቸው የተለየ መገለጫ ባህሪ እንዳላቸው ከላይ ከቃኘናቸው ትምህርቶች መረዳት እንችላለን። ሰዎችን ስናከብር ወይም ሰዎች እኛን ሲያከብሩን የሚሰማን ስሜት የተለየ እና ደስ የሚል ነው። ሌሎችን የሚያከብር ሰው የሚያሳየቸው ባህሪያት ጨዋ፤ ታጋሽ፤ ተንከባካቢ ፤ጥሩ አድማጭ ፤አፍቃሪ፤ ሀላፊነት የሚሰማው፤ ቻይ እና ትግስተኛ ነው።



ምሰል 1.9 የተከበሩ ሰዎች ባህሪያት

ተግባር 2.12

1. የተከበረ ሰው ባህሪያትን ጥቀስ?
2. ሌሎችን ከማክበር አንፃር የእናንተን ባህሪ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ።

2.5. ሌሎችን አለማክበር የሚያስከትለው ጉዳት

የማነቃቂያ ጥያቄ

ሌሎችን የማክበር ተቃራኒው ምንድን ነው?

የመከባበር ተቃራኒው አለማክበር ነው። ለሌሎች ሰዎች አክብሮትን አለማሳየት አለማድነቅ ትህትናን አለማሳየት ወይም ለሌላ ሰው አለመጨነቅ ማለት ነው፡፡ የሰዎችን ስሜት ፍላጎት ነፃነት ክብር ሰብአዊነትን ከግምት ውሰጥ ሳይስገቡ ሰዎችን መሳደብ ጨዋነት

የጎደለው ተግባር ማከናወን እና አፀያፊ ተግባር መፈፀምን ያመላክታሉ።።



ምስል 2.5 ሌሎችን ለማክበር

እነዚህ ባህሪያት እና ድርጊቶች በርካታ ተጽእኖዎች አሏቸው።። ለምሳሌ

•ጨዋነትን እና ክብርን ይጎዳል።

- የግንኙነት መንገዶችን ያበላሻል፣
- ትብብርን ይጎዳል።
- ጓደኝነትን ያበላሻል
- ጥላቻን ወይም ጤናማ ያልሆነ ግንኙነትን ያሳድጋል፣
- በማህበረሰቡ ውስጥ ሰላማዊ የሆነ ግንኙነት እንዳይኖር ያድርጋል።።

ተግባር 2.13

1. ለራስህ ክብር አለመስጠት በማህበረሰብ ውስጥ የሚያመጣው ወይም የሚያስከትለውን መዘዝ ዘርዝሩ?
2. ሌሎችን የማክበር እና አለማክበር ጽንሰ-ሀሳቦችን አነጻጽሩ?

የምዕራፍ ማጠቃለያ

ይህ ምእራፍ ሌሎችን ስለማክበር የሚያብራራ ነው። ሌሎችን ማክበር ማለት ለሰዎች ዋጋ ከመስጠት እና ሰውን ከማክበር ይጀምራል። ሌሎችን ስናከብር የምናሳያቸው ባህርያት ሰላምታ፤ ጨዋነት፤ ጥሩ አድማጭ መሆን እና ሌሎችንም ያካትታል። በህብረተሰቡ ውስጥ ክብር መስጠት የሚገባን ለማን ነው የሚለውንም በሰፊው አይተናል ለምሳሌ ለሽማሌዎች ለእድሜ ባለፀጋዎች ፤ ለሃይማኖት አባቶች ፤ለመምህራን፤ለጎረቤቶች እና ለክፍል ጓደኞቻችን ክብር ማሳየት እንዳለብን አይተናል።

ቁልፍ ቃላት

አክብሮት፡- የሌላን ሰው የመኖር አስፈላጊነት መረዳት ወይም ጥሩ ስሜት መኖር

ጎረቤት፡- ከሌላ ሰው አጠገብ የሚኖር ሰው።

ዘመድ፡- በቤተሰብዎ ውስጥ ያሉ በደም የተሳሰሩ ሰዎች።

የተከበረ፡- ክብር የሚገባው

የምዕራፉ መልመጃ ጥያቄዎች

ክፍል1፡- አ.ርፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. ሌሎችን ማክበር ለራስ ብቻ ክብር የመስጠት ሁኔታን ያመለክታል።
2. በዕድሜ ትልልቅ የሆኑ ሰዎች መከበርን ይሻሉ፡፡
3. የሃይማኖት መሪዎች በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ናቸው።
4. ጎረቤቶችን ማክበር ሰላማዊ ግንኙነትን ያመጣል፡፡
5. ሌሎችን አለማክበር በማህበረሰቡ ውስጥ የግጭት መንስኤ ሊሆን አይችልም።

ክፍል II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘዉን ምረጡ.

1. ከሚከተሉት ውስጥ ሌሎችን ስለማክበር ስህተት የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. የሰውን ክብር ማክበር
   ለ. ማመስገን
   ሐ. የሌሎችን ሀሳብ ችላ ማለት
   መ. ጨዋ መሆን
2. ከሚከተሉት ውስጥ የእድሜ ባለፀጋዎችን ስለማክበር ስህተት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ጨዋ መሆን

ለ. ሰዎች ሲነጋገሩ ማቋረጥ

ሐ. ለሰዎች በአክብሮት ምላሽ መስጠት

መ. የሽማግሌዎችን ምክር መቀበል

3. ከሚከተሉት ውስጥ ሌሎችን የማክበር ጥሩ ባህሪይ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. መጥፎ ባህሪ

ለ. ችላ ማለት

ሐ. ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት

መ. ማዳመጥ

4. ከሚከተሉት ውስጥ ሌሎችን አለማክበር መገለጫ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. ትብብርን መጉዳት

ለ. ጥላቻን ማራመድ

ሐ. ሰላማዊ አብሮ መኖርን ችላማለት

መ. ሁሉም መልስ ነው

ክፍል III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ጻፉ።

1. የእድሜ ባለፀጋዎችን ከምናከብርበት መንገድ ቢያንስ ሦስቱን ጥቀሱ?

2. ሌሎችን የከማክበር አስፈላጊነት ወይም ጥቅሞች ውስጥ ቢያንስ ሶስት ጻፉ?

3. ሌሎችን አለማክበር የሚያስከትለውን ጉዳት ዘርዝር?

ምዕራፍ ሦስት

እኩልነት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፡-

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-

- **እኩልነትን መግለፅ ትችላላችሁ፡፡**
- **በትምህርት ቤት እና በማህበረሰቡ ውስጥ የእኩልነት አያያዝን አስፈላጊነት ዋጋ ትሰጣላችሁ፡፡**
- **በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ ፍትሃዊ አያያዝን ማሳየት ትችላላችሁ፡፡**
- **በግለሰቦች ወይም በቡድኖች ላይ እኩል ያልሆነ አያያዝ የሚያስከትለውን ውጤት ትዘረዝራላችሁ፡፡**

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የእኩልነት ትርጉምን ያስተዋውቃችኋል። እንዲሁም በትምህርት ቤት እና ማህበረሰብ ውስጥ የእኩልነት አስፈላጊነት ላይ ግንዛቤን ይፈጥራል፡፡ እንዲሁም የጾታ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት እና የባህል እኩልነት የሚሉ ፅነሰ-ሃሳቦች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ያወያያችኋል፡፡በመጨረሻም የእኩልነት አያያዝን አስፈላጊነት እና የእኩልነት መንደል ውጤቶችን ይዘረዝራል፡፡

3.1. እኩልነት ምንድን ነው?

የማነቀቂያ ጥያቄ

1. እኩልነት የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ስትሰሙ ወደ አእምሮችሁ ምን አይነት ሀሳቦች ይመጣሉ ናቸው?

2. እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?

እኩልነት ማለት አንድ አይነት ደረጃ ያላቸውን ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ተመሳሳይ መብቶችን፤ ጥቅሞችን እና ሃላፊነቶችን እኩል ተደራሽ ማድረግ ማለት ነው፡፡ የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ብቻ ተመሳሳይ መብቶች አሉት፡፡ተመሳሳይ የሙያ ደረጃ ያላቸው ግለሰቦችም እኩል ጥቅሞችን እና መብቶችን የመጠየቅም ሆነ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ በተጨማሪም እኩልነት ማለት እኩል መብቶችን እና ጥቅሞችን ዜጎች እንዲያገኙ ማመቻቸት እና እድሎችንም እኩል እንዲጠቀሙ ማድረግ ማለት ነው፡፡ የእኩልነት መብቶች ሲተገበሩ ዘርን ፤ሀይማኖትን፤ ያታን፤ ቋንቋን ፤ማኅበራዊ ሁኔታን እና ሌሎችንም መሰረት ያደረጉ መሆን የለባቸውም፡፡ሰለዚህ ሀብት የማፍራት መብት፤ትምህርት የማግኘት መብት እና ሰብአዊ ክብርን የማግኘት መብት በእኩል ለሁሉም ዜጎች እኩል ተደራሽ መሆን አለባቸዉ፡፡

ታሪክ

ቡቤ በትምህርት ቤት በጣም ታዋቂው ልጅ ነበር። በውድ ጫማዎች፣ ሱሪዎች እና በቁመናው በጣም ይታወቅ ነበር። እሱ በሁሉም ሰው የተከበረ እና የተደነቀ ነበር ይኸውም ውድ መጫወቻዎቹ እና ልብሶቹ የትምህርት ቤት ልጆችን ለመማረክ በቂ ነበሩ። ይሁን እንጂ ጓደኞቹን በሚመርጥበት ጊዜ የተወሰኑ መመዘኛዎች ነበሩት ስለዚህ የሱ ጓደኛ ለመሆን ከፍተኛ የክፍል ደረጃ ያስፈልግህል እንዲሁም ያማረር ውበት የሌለህ ወይም የሀብታም ልጅ ካልሆንክ ፣እባክህን ጊዜዬን ካንተ ጋር ማባክን አልፈልግም ብሎህ ይሄዳል።

አንድ ቀን ዱዱ የሚባል አዲስ ልጅ ወደ ትምህርት ቤቱ ሲቀላቀል ነገሮች ሁሉ ተቀያየሩ የዱዱ ብልህነት እና ስብዕና ሁሉንም ሰው መሳብ ጀመረ።

ዱዱ በተለይ ከመጀመሪያው የፈተና ክፍለ ጊዜ በኋላ ተወዳጅ ሆነ ዱዱ በትምህርቱም ሆነ በክበባት እንቅስቃሴ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ መሳተፍ ጀመረ አሁን ሁሉም ሰው ዱዱን መፈለግ ጀመረ ዱዱ እንደ ቡቤ ይሄ ደሀ ነው ወይም ሃብታም ነው ብሎ የሚመርጥ ልጅ አልነበረም ከሁለት ቀን በኋላ የቡቤ ልደት ቀን በመሆኑ የቅርብ ጓደኛው ማና ወደ እሱ መጣ።

ማና ቡቤ ለልደትህ ዱዱንም መጋበዝ አለብህ አለዉ፣ቡቤ እኔ አሱን መጋበዝ አልፈልግም ምክንያቱም የሚይዘው ርካሽ የምሳ እቃ አለባበሱም ጥሩ አይደለም የሚያመጣውም ምግብ ምንም ጣዕም የለውም ሰለዚህ ከእኛ ጋር ሊመሳሰል ሰለማይችል መጋበዝ አልፈልግም አለ።

ማናም አየህ ቡቤ ሁሉም ሰው ዱዱን ይወደዋል አለዉ፤ቡቤም ተው ባከህ የሚወዱት ሰለሚያዝኑለት ነው አለዉ፤ቡቤም ሰዎች ሁሉ ዱዱን መውደዳቸውን ሲመለከት የሰው ልጅ ባለው አቋም በሚለብሰው ልብስ ሊመረጥ እንደማይችል ሰዎችን ባለበት ሁኔታ መቀበልን ተረዳ። ከዚያ በኋላ ቡቤ ዱዱን ይቅርታ ጠይቆ ለሰዎች ዋጋ መስጠት ያለብን በሚበሉት ወይም በሚለብሱት ነገር አለመሆኑን ተረዳ። እንዲሁም ሰብዓዊነት እንደሚቀደምም አወቀ።

ተግባር 3.1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ከላይ ካለው ታሪክ ምን ተማራችሁ?
2. አንድን ሰው እንዳለ መቀበል እና ማክበር ከፍተኛ የሆነ ሞራላዊ መገለጫ ነዉ ብላችሁ ታስባላችሁ?

3.2 በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ ያለ እኩልነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

1.ተማሪዎች በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያላችሁን የእኩልነት መብት ጥቀሱ?

2.ተማሪዎች በማህበረሰባችሁ ውስጥ ያላችሁን የእኩልነት መብቶች ጥቀሱ?

ተማሪዎች በትምህርት ቤትም ሆነ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሊከበሩላችሁ የሚገባችሁ መብቶች አላችሁ። ከነዚህም ውስጥ ጥያቄ የመጠየቅ ፤ለጥያቄዎቻቸው መልስ የማግኘት ፤ከመደበኛ ትምህርት ውጪ በክበብ

የመሳተፍ ፤ እና የትምህርት ቤት ንብረቶችን እኩል የመጠቀም ናቸው፡፡ ሌላው ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ልትወጪቸው የሚገቡ ሀላፊነቶች የሚከተሉት ናቸው የትምህርት ቤቱን ህግ እና ደንብ ማክበር፤ለሌሎች ተማሪዎች አርአያ መሆን የቤት ሥራቸውን እና የክፍል ስራቸውን በአግባቡ ማከናወን እነዚህ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ግደታዎች ናቸው፡፡

ተግባር 3.2.

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ

3. በትምህርት ቤታቸሁ ውስጥ ሊከበሩ የሚገባቸው አንዳንድ የተማሪ መብቶችን ጥቀሱ?

4. በትምህርት ቤት ውስጥ መወጣት ያለባችሁ ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

3.2.1. የጾታ እኩልነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

የወንድ እና የሴት ልጆች እኩልነት ስንል ምን ማለታችን ነው?



ምስል3.1. ሴት ልጅ እና ወንድ ልጅ እኩል ናቸው

ሥረዓተ ጾታ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለውን በማህበራዊ ፤ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያለውን እኩልነት ያመለክታል። ቀደም ሲል ወንዶች እና ሴቶች ንብርት የማፍራትና ባለቤት የመሆን ፤ ከወንዶች እኩል ትምህርት የማግኘት እና በፖለቲካ እኩል የመሳተፍ መብት አልነበራቸውም።

የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ማለት በወንዶች እና በሴቶችን መካከል የሚገኝ የእኩልነት አይነት ነው። ወንዶች እና ሴቶች መሠረታዊ መብቶቻቸውን ማለትም የመማር፤ የመጫወት፡ የሥራ እድል የማግኘት መብቶች ያለምንም መሸራረፍ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ማለት ነው። ሴቶች የህብረተሰቡ ግማሽ አካል በመሆናቸው ከላይ የተዘረዘሩትን መብቶች እኩል ማግኘት ይኖርባቸዋል።ሁሉም ኢትዮጵያዊ የፆታ እኩልነት እንዲረጋገጥና አድሎአዊነት እንዲቆም የራሱን አስተዋፅኦ ማድረግ ይኖርበታል። ምክንያቱም የፆታ እኩልነትን

መቀበል እና ማክበር ለአንድ ማህበረሰብ የሚሰጠው ጥቅም የጎላ በመሆኑ ነው። ከዚህ በመነሳት ሴቶችን በኢኮኖሚያዊ፤ በማህበራዊ እና በፖለቲካ ማብቃት በኑራቸው ላይ የራሳቸውን ውሰኔ መወሰን፤ የራሳቸውን ጉዳይ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ማሰፈፀም አንዲችሉ ያደርጋቸዋል።ስለዚህ በሀገር ውስጥ የፆታ እኩልነት ሲረጋገጥ ማህበረሰባችን ብዙ ጥቅሞችን ማግኘት ይጀምራል ለምሳሌ የተረጋጋ፤ደህንነቱ የተረጋገጠ እና የበለፀገ ማህበረሰብ እንዲኖር ያደርጋል። በተጨማሪም ደስተኛ እና የተማረ ዜጋን ማፍራት እንችላለን።

ስለ ፆታ እኩልነት ስንነጋገር፡-

- በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለውን የትምህርት ተደራሽነት ልዩነት ማስተካከል
- በፖለቲካ ውስጥ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለውን ልዩነት ማስተካከል እና የተሳትፎ እና የስራ እድሎችን ማስፋት
- ሴቶች መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ መደገፍ

ተግባር 3.3

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

1. ተማሪዎች በባህላዊ መልኩ የወንዶች ስራ ተብለው የተመደቡ እና የሴቶች ሥራ ተብለው የተመደቡትን ዘርዘሩ?
2. በወንዶች እና በሴቶች ሊሰሩ የሚችሉ ነገር ግን በተለምዶ ሴቶች ብቻ የሚሰሩትን ሥራዎች ዘርዝሩ

3. በሴቶች እና በወንዶች ሊሰሩ የሚችሉት ነገር ግን በተለምዶ የወንዶች ስራ ተብሎ የሚታሰቡ ሥራዎችን ዘርዝሩ?

3.2.2. የቋንቋ እኩልነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

*** የቋንቋ እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?**

ቋንቋ ባህላችንን የምንገልፅበት አንዱ መንገድ ነው። የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለመግባባት የተለያየ ቋንቋዎችን ይጠቀማሉ። ቋንቋን በመጠቀም የእለት ተእለት ተግባራችንን እና ስሜታችንን እንገልፃለን።ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች እኩል ናቸው በዚህ መሰረት የሚጠቀሟቸው ቋንቋዎችም እኩል ናቸው ማለት ነው። ስለዚህ ሁሉም ማህበረሰብ የሚናገረው ቋንቋ በሌሎች ዘንድ እንዲከበርለት ይፈልጋል፤ እራሱ በሚናገረው ቋንቋ የተለያዩ አገልግሎቶችን ማግኘት ይፈልጋል ለምሳሌ ለትምህርት ፤ ለስነ-ፅሁፍ ፤ ለፍረድ ቤት አገልግሎት የማዋል መብት አላቸው።በተጨማሪም የፍትህ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አላቸው ከዚህም በላይ ሰዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋዎች በተጨማሪ ሌሎችን ቋንቋዎች የመማር መብት አላቸው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አለ እያንዳንዳቸው የራሳቸው ቋንቋ አሏቸው ለምሳሌ፣ ከመወለዳችን ጀምሮ በቤተሰባችን እና በአካባቢ ውስጥ የሚነገሩ ቋንቋዎችን እንማራለን። ያወቅነውን የመጀመሪያ ወይም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስንናገር ምቾት ይሰማናል፤ ስለዚህ ከሌላ

ቦታ የመጡ ሰዎችም የራሳቸውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሲናገሩ ምቾት ይሰማቸዋል ማለት ነው።።

ሁሉም ቋንቋዎች እኩል እና አስፈላጊ ናቸው በሌሎች ሰዎች የሚነገሩ ቋንቋዎችን ማክበር አስፈላጊ ነው።። ይኸውም ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ሰዎችን በአግባቡ ለመያዝ እና እኩልነትን ለማረጋገጥ ይረዳል።።

ተግባር 3.4

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

1. ሁሉም ቋንቋዎች እኩል ናቸው ብላችሁ ታስባላቹ? ለምን? በክፍሉ ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ ተወያዩበት.
2. በአካባቢዎ ያሉ ሰዎች የሚናገሩትን ቋንቋዎች ዘርዝሩ።

3.2.3. የሃይማኖት እኩልነት



ምስል 3.2. የተለያዩ የሀይማኖት ተቋማት

የማነቃቂያ ጥያቄ

*** የሃይማኖት እኩልነት ስንል ምን ማለታችን ነው?**

ሃይማኖት የእምነት እና የአምልኮ ስርአት ነው፡፡ የሃይማኖት እኩልነት ማለት ሁሉም ዜጋ የሚፈልገውን ሃይማኖት የመከተል፤የመስበክ እና የማስተማር መብት አለው፡፡ በመሆኑም ሁሉም ዜጋ የሌላውን ሃይማኖት መናቅ ወይም እንዳያመልክ ማድረግ አይችልም፡፡ በመሆኑም አንዱ የሌላዉን ሃይማኖት ማክበር ይጠበቅበታል፡፡ ኢትየጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶች የሚገኙባት ሀገር ስትሆን እነዚህም ክርስትና፤ እስልምና፤ፕሮቴስታንት፣ዋቄፈታና የመሳሰሉት ሲሆኑ ሁሉም ሃይማኖቶች ተከባብረው በሰላም የሚኖሩባት ጥሩ ታሪክ ያላት ሀገርም ነች፡፡ ከላይ ከጠቀስናቸው ሃይማኖቶች መካከል የትኛውም ሃይማኖት የበላይ ወይም የበታች አይደለም፡፡ስለዚህ ሁሉም ዜጋ የፈለገውን ሃይማኖት የመከተል፤የማምለክ እና የመስበክ መብት አለው፡፡ይህንንም ሲያደርግ የሌላ ሃይማኖት የሚከተሉ ሰዎችን መብት ሳይነካ መሆን አለበት፡፡ ለሰዉ ልጆች ሁሉ የሃይማኖት ነፃነት ካልተከበር በሰላም ለመኖር አስቸጋሪ ነው ሰዎች የፈለጉትን ሃይማኖት የመከተል መብት እና የሌሎችን ሃይማኖት የማክበር ዋስትና መስጠት በሀገር ላይ መረጋጋትን፤ደህንነትን ፤ሰላምን እና ልማትን ያመጣል፡፡

በሃይማኖቶች መካከል የጋራ መግባባት እንዲኖር የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ነው

- **የሌሎች ሰዎችን ሀይማኖት ማክበር እና ልዩነቶችን በውይይት መፍታት**
- **ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታት ካልተቻለ በህግ መሰረት መፍታት**

• አብሮ ለመኖር የሀይማኖት ልዩነት ያለመግባባት መነሻ እንዳይሆን መቻቻል

ተግባር 3.5

በቡድን በመሆን በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

1. የሁሉንም ሃይማኖቶች በእኩልነት ማክበር ምን ጥቅም አለው?
2. ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ የዜጎች ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?
3. በሀማኖቶች መካከል መቻቻል አለመኖር ለጋራ ጥቅም ጎጂ ነው ብላችሁ ታስባላቹ?
4. ሊፈጠሩ የሚችሉ ሀይማኖታዊ ግጭቶችን እንዴት ማስወገድ ወይም መቀነስ እንችላለን?

3.2.4. የባህል እኩልነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

1. የባህል እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ተማሪዎች! ከሚከተለው ሥዕል ምን ተረዳችሁ?



ምስል 3.3፡ የተለያዩ ባህሎችን የሚያሳይ ምስል

ባሕል የአንድ ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ መገለጫ ነው፡፡ ቋንቋ እና ሃይማኖት የአንድ ባህል መገለጫዎች ናቸው፡፤ በተጨማሪም ባህል በአነጋገር፤ በአለባበስ፤ በአመጋገብ እንዲሁም ደስታ እና ሀዘናችንንም የምንገለፅበት ሌላኛው መንገድ ነው፡፡ ባህል ሰፊ እና ጥልቅ የሆነ ጽንሰ ሀሳብ ነዉ፡፡

ኢትየጵያ የተለያዩ የባህል ልዩነቶች ያሉባት ሀገር እነደመሆንዋ መጠን እነዚህ ባህሎች ከአካባቢ አካባቢ የተለያዩ ናቸው፡፡ ሁሉም ባህሎች የራሳቸው ልዩነቶች ቢኖራቸውም የአካባቢው የአኗኗር ዘይቤ መገለጫዎች በመሆነቸዉ የትኛውም ባህል የበላይ ወይም የበታች አይደለም፡፡ስለዚህ ሁሉም ባህሎች እኩል ናቸው ማለት ነው፡፡ባህል በማህበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ እድገቶች ምክንያት በየጊዜው ይለዋወጣል፡፡

ኢትየጵያ ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ያሉባት ሃገር ስትሆን ሁሉም ብሄረሰቦች የራሳቸው የሆነ የአለባበስ፤ ባህላዊ የቤት አሰራር፤ ባህላዊ ምግብ እና ባህላዊ የአጨፋፈር ስልት አላቸው ፡፡

እነዚህ የተለያዩ ባህሎች አንድ ላይ ሲታዩ ማራኪ እና አስደሳች ናቸው፡፡

ተግባር 3.6.

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

1. ባህል ምንድን ነው?
2. በአካባቢያችሁ ያለው ማህበረሰብ የሚጠቀምባቸውን ባህላዊ ልምዶች ይዘርዝሩ።

3. የሚከተለውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ ገልብጡ እና በአከባቢያችሁ የሚከናወኑ ጎጂና ጠቃሚ ልማዶችን በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ ።

ተ.ቁ	ጠቃሚ ልማዳዊ ድርጊቶች	ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች
1		
2		
3		

በኢትዮጵያ የተለያዩ ጥሩ እና መጥፎ ልማዳዊ ድርጊቶች አሉ። ከእነዚህም ጥቂቶቹ ከታች የተዘረዘሩትን ያካትታሉ።

ሀ. ጥሩ ልማዳዊ ድርጊቶች

- እድሜ ባለፀጋዎችን ማክበር
- እድር እና እቁብ
- የተቸገሩትን መርዳት
- በጋራ ሥራን መስራት
- እንግዳ ተቀባይነት ወዘተ.

ለ. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

- የሴት ልጅ ግርዛት

*ያለ እድሜ ጋብቻ

* በሀዘን ጊዜ አካልን መቧጨር

* አካልን በሹል ነገር መቁረጥ

* ገንዘብንና ጊዜን ያለአግባብ ማባከን

* ጠለፋ ወዘተ

3.3. የእኩልነት አያያዝ አስፈላጊነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

የእኩልነት አያያዘ ጽንሰ-ሐሳብን ግለጹ?

እኩልነት በየትኛውም ማህበረሰብ አስፈላጊ ነው። እኩልነት ሰዎችን ሁሉ በተመሳሳይ ሁኔታ የማየት እና የእኩል ተጠቃሚነትን ያለምንም አድሎ እና መገለል ተጠቃሚ መሆን ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ እኩልነት በሰዎች መካከል ተመሳሳይ የትምህርት እድል እና ተሳትፎ በዘር ፤ በቀለም፤ በፆታ ፤ በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ እኩል ማግኘት ማለት ነው። በሰዎች መካከል እኩልነት ከሌለ በግለሰቦችም ሆነ በሀገር ላይ የሚያመጣው አደጋ ከፍተኛ ነው። ሰለዚህ ሁሉም ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ እኩል ተጠቃሚ መሆን አለበት ማለት ነው። ለምሳሌ በአንድ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በተመሳሳይ መንገድ፤ በፍታሃዊነት እኩል የመስተናገድ እድል ሊኖራቸው ይገባል። የሰው ልጆች በእኩልነት ከተያዙ እና እኩል እድል ከተሰጣቸው በማህበረሰቡ ውስጥ በኢኮኖሚም ሆነ በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም የባለቤትነት ስሜት እና ለለውጥ እና ለእድገት የሚተጉ ይሆናሉ።

ተግባር 3.7

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

1. **የእኩል አያያዝን ዋና አስፈላጊነት ዘርዝሩ።**
2. **እኩልነትን በተግባር ሊተገበርባቸዉ የሚገባ ቦታዎችን ግለጹ።**

3.4. የእኩልነት አለመኖር መዘዞች

የማነቃቂያ ጥያቄ

- **የእኩልነት አለመኖር አሉታዊ ተፅእኖ አለው ብላችሁ ታስባላችሁ? መልሳችሁ አለ ከሆነ ምን ምን ናቸዉ?**

የእኩልነት አለመኖር አድሎ እና መገለል መኖርን ያሳያል። እንዲሁም ሰላም እንዳይኖር ያደርጋል፤ በዚህም ምክንያት በሃገር እድገት ላይ ተፅዕኖ ያስከትላል። በእኩልነት ያልተያዙ ሰዎች ወይም ቡድኖች መብታቸውን መጠየቅ ይጀምራሉ፤ የእኩል እንሁን ጥያቄያቸው በትክክል ካልተመለሰ ደግሞ ወደ ግጭት እና ጦርነት ሊያመሩ ይችላሉ። በዚህም ምክንያት የተለያዩ ችግሮች ይከሰታሉ። እነሱም የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ግጭት፣ ኢፍትሃዊነት፣ አለመረጋጋት፣ ሁከት፣ እና በቡድን እና በግለሰቦች መካከል አሉታዊ ግንኙነቶች እነዲኖሩ ያደርጋሉ።

ተግባር 3.8

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

1. **አድሎአዊ አስራርን እንዴት መቀነስ እንችላለን?**
2. **አድሎአዊ አስራር በስፋት የሚታይባቸዉን ቦታዎች ጥቀሱ?**

የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የእኩልነትን ትርጉም እና ዓይነቶች ተምረናል ። እኩልነት ማለት ፍፁም ተመሣሣይነትን አያሳይም። እኩልነት ማለት ተመሳሳይ መብቶችን ማለትም ጥቅሞች, እና እድሎችን በእኩልነት መጠቀም ማለት ነው። እኩልነት መሰረታዊ የሰው ልጅ መብት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሀሉም ዜጎች እኩል የሆነ ኢኮኖሚያውና ፖለቲካዊ መብቶች አላቸው። ይህም ሲተገበር ያለምንም መድሎና መገለል ለሁለም ዜጋ መሆን አለበት ። ኢኮኖሚያዊ እኩልነት ማለት እኩል የስራ እድል የማግኘት መብት ሲሆን ፖለቲካዊ እኩልነት ማለት በፖለቲካ ተሳትፎ ውስጥ ተመሣሣይና እኩል እድል የማግኘት መብት ማለትነው።

ስርዓተ ጾታ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለ ልዩነት ሲሆን ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ ነው።የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት የሚያመለክተው የወንዶች እና የሴቶች እኩል እድሎች እና መብቶቻቸውን መጠቀም ማለት ነው። ባሕል የአኗኗር ዘይቤ መገለጫ ነው።የባህል ልዩነት ብዙ ጥቅሞች አሉት ምክንያቱም እያንዳንዱ ባህል ለሀገር እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል። የባህል ልዩነቶችን ስናከብር ባህሎቻችን ተጠቃሚ ይሆናሉ።

የሌሎችን ባህል አለማክበር ወደ ግጭት ሊያመራ ይችላል። ልዩነትን ማክበር እና ባህሎችን በእኩል ማየት ይኖርብናል።

ቁልፍ ቃላት

ባህል፡- የአንድ ማህበረሰብ ልማዶች፣ እምነቶች፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ባህላዊ ልምዶች፣ ቋንቋ እና ሃይማኖት ወዘተ

"ደቦ" ወይም "ወንፈል"፡ በጋራ ሥራን የመሥራት ልምድ

አድሎ፡ ሰዎችን በዘር፣ በእድሜ፣ በቀለም እና በመሳሰሉት መሠረት አድርጎ ኢፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለመለያየት የሚደረግ ተግባር ነው፡፡

ልዩነት፡ በሰዎች መካከል በባህል፣ በሃይማኖት፣ቋንቋዎች ልዩነቶች ወዘተ.

እኩልነት፡- ምንም አይነት አድሎ ሳይደረግ ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት እና ሃላፊነቶችንም የመወጣት መብት

ስረዓተ ጸታ፡ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው ልዩነት በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣እና የፖለቲካ ተሳትፎ

ሃይማኖት፡ የተደራጁ እምነቶች፣ ልምዶች እና ሥርዓቶች ስብስብ ነው።

መብት ፡ ጥቅሞችን የማግኘት

መረጋጋት: ሰላም መስፈን

የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ መልመጃዎች

ቀጥሎ የቀረቡ የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ ጥያቄዎችን ስሩ፡፡

ክፍል አንድ፡ ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እዉነት ስህተት ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. እኩልነት በሰዎች መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ያሳያል።
2. ልጆች በትምህርት ቤትም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ እኩል መብት አላቸው።
3. የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን እኩልነት ያመለክታል፡፡
4. የዲሞክራሲ ስርአት አንዱ መገለጫ የቋንቋ እኩልነት ነው።

ክፍል ሁለት ፡- በሀ አምድ ስር ያሉትን ቃላትና ሀረጎች በለ አምድ ስር ካሉት ጋር አዛምዱ

አምድ ሀ	አምድ ለ
1. መልካም ሥነ ምግባር	ሀ. የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት
2. የወንድና የሴቶች እኩልነት	ለ. የእድሜ ባለፀጋዎችን ማክበር
3. የእምነት እኩልነት	ሐ. የሃይማኖት እኩልነት
4. የብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ማንነት መግለጫ፣	መ. ቋንቋ

ክፍል ሦስት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. ከሚከተሉት ውስጥ በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎችን እኩልነት የሚያሳየዉ የቱ ነው?

ሀ. ጥያቄዎችን መጠየቅ

ለ. ግላዊ ሃሳብን በሌሎች ላይ መጫን

ሐ. ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በክበባት እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ

መ. በተማሪ ጉዳዮች ውስጥ መሳተፍ.

2. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ቋንቋ እውነት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ሌሎች ቋንቋዎችን መማር ምንም ጥቅም የለውም

ለ. አንዳንድ ቋንቋዎች ከሌሎች ቋንቋዎች የተሻሉ ናቸው።

ሐ. ሁሉም ቋንቋዎች እኩል ናቸው።

መ. የቋንቋ እኩልነት አለመከበር ችግር አያመጣም።

3. ከሚከተሉት ውስጥ የባህል ልዩነትን በተመለከተ ትክክል ያለሆነዉ የትኛው ነው?

ሀ/ የልዩነት መኖር ወደ ግጭትና ጦርነት ይመራናል።

ለ. የተለያዩ አይነት የአለባበስ ዘይቤዎችን እና ዳንሶች መኖሩ ውብ ነው።

ሐ. እያንዳንዱ ባህል ለጎብረተሰቡ አንዳንድ እሴቶችን ያበረክታል።

መ/ የተለያዩ ባህሎች መኖር የቱሪስቶችን ትኩረት ይስባል

4. ከሚከተሉት ውስጥ የሰዎችን ባህል የሚያሳየው የትኛው ነው?

ሀ. የደስታ እና የሀዘን መግለጫ

ለ. የአለባበስ ዘይቤ

ሐ. የምግብ አዘገጃጀት

መ. ሁሉም ትክክል ናቸው።

ክፍል አራት. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ጻፉ።

1. ልጆች በትምህርት ቤት እና በማህበረሰቡ ውስጥ ሊያገኟቸው የሚችሏቸውን ዋና ዋና መብቶች ዘርዝሩ።

2. ስለ ዕታ እኩልነት ጥቅሞች ሁለት ነጥቦችን ዘርዝሩ።

3. የሥርዓተ-ዕታ አለመመጣጠን ዋነኛው ምንጭ ምንድን ነው?

4. የእኩልነት መጓደል የሚያመጣው የተለመዱ ውጤቶች ምንድን ናቸው? ዘርዝሯቸው

ምዕራፍ አራት

ጤናማ ማህበራዊ ሕይወት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፡-

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ፡፡

- **የጤናማ ማህበራዊ ህይወት ጽንሰ-ሀሳብን ታብራራላችሁ፤**
- **የጤናማ ማህበራዊ ህይወት ባህሪያትን ትገልጻላችሁ፤**
- **ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ለህብረተሰብ መስተጋብረ የሚያበረክተዉን አስተዋፅኦ ታደንቃላችሁ፤**
- **ጤናማ ማህበራዊ ህይወትን ታንፀባርቃላችሁ፤**
- **ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን ትለያላችሁ፤**

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ስለ ጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ምንነት እና መገለጫ ባህሪያት ላይ ግንዛቤን ይፈጥርላችኋል፡፡ በተመሳሳይ ጤናማ ማህበራዊ ህይወትን ማዳበርና መኖር ስለሚያስገኘዉ ጠቀሜታ እና ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን በዝርዝር ይመለከታል፡፡

4.1. የጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ጽንሰ-ሀሳብ

የማነቃቂያ ጥያቄ

1.ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ማለት ምን ማለት ነዉ?

2. ጤናማ ማህበራዊ ህይወት እንዲኖር የምንከተላቸው መንገዶች ምን ምን ናቸዉ?

ሰው ማህበራዊ ፍጡር ነዉ፣ ስለዚህ ለጤንነታችንና ደህንነታችን ሲባል ትዉዉቅና ትውውቅና ግንኙነት ሊኖረን ይገባል። ጤናማና የተመጣጠነ ምግብ ብንመገብ፣ በቂ እንቅልፍ ብንተኛ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ብንችል እንኳ ማህበራዊ ጤንነት የሌለን ከሆነ ከአጠቃላይ ጤናችን ወሳኝ ክፍል ይጎድላል ማለት ነዉ። በመሆኑም ስለ ማህበራዊ ጤንነት አስፈላጊነት ማወቅ እና ዋጋ መስጠት ይኖርብናል። ጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ማለት ከሌሎች ጋር የመግባባትና እና ትርጉም ያለው መስተጋብር የመመስረት ችሎታ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል።

ከማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር ራሳችንን የምናጣጥምበት ችሎታ ከጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ጋር ተያይዞ ሊታይ ይችላል። ማህበራዊ ግንኙነቶች በአእምሯዊና በአካላዊ ጤንነታችን እና በአጠቃላይ ህይወታችን ላይ ተፅእኖ አላቸው። ለምሳሌ፡- በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ጥሩ የሐሳብ ልውውጥና ተግባቦት፣ እርስ በርስ መከባበር፣ መቻቻል፣ የመረዳዳት እና ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህል ሊኖር ይገባል። እነዚህ ጤናማ ማህበራዊ ህይወት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ስለመኖሩ ጠቋሚዎች ናቸው። ከቤተሰብና ጓደኞች ጋር ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር የጤናማ ማህበራዊ ህይወት መገለጫ መንገድ ነዉ።



ምስል 4.1: ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ያላቸዉ ልጆች

ተግባር 4.1

1. ከሥዕሉ ምን ተረዳችሁ?
2. ስእሉ ከጤናማ ማህበራዊ ህይወት ጋር የተያያዘ ነው?

የአቱሞ ህይወት

አቱሞ የ11 አመት ልጅ ሲሆን የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው። አንድ ቀን ትምህርት ቤታቸው ወደ አዞ እርባታ ጣቢያ ትምህርታዊ ጉዞ ለማድረግ ወሰነ። ጉዞው የአካል ጉዳተኛ የሆነውን አቱሞን ጨምሮ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎችን በሙሉ የሚመለከት ነበር። ወደ ጉብኝቱ ስፍራ እንደደረሱ በጣም ውስን ማህበራዊ ሕይወት የነበረዉ አቱሞ ራሱን በአቅራቢያው ካሉ ተማሪዎች አገለለ። በዚሁ ምክንያት ለብርቱ ድብርት ወይም ድባቴ ከመዳረጉም አልፎ ከፍተኛ የጤና ችግር ገጥሞታል። የልብ ጓደኛውን ታጋዩን እስከሚያገኝ ድረስ ያለማቋረጥ ይጨነቅ ነበር።

ምርጥ ጓደኛውን ካገኘ በኋላ ድባቴዉ እና የመንፈስ ጭንቀቱ መቀነስ ጀመረ። አብረው ጊዜ ማሳለፍና መመካከር በመጀመራቸዉ የአቱሞ ማህበራዊ ሕይወቱና ከጭንቀት ጋር ተያይዞ የነበረበት የጤና ችግር ጥሩ መሻሻል አሳየ። አቱሞ ከታጋዩ ጋር ጓደኝነት መመስረቱ እጅግ በጣም ጠቅሞታል። በዚሁ ግኑኝነት ምክንያት የፍቅርና የመንከባከብ ስሜቱን ከማዳበሩም በላይ ከጓደኛዉና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብና መግባባት ችሏል።

ተግባር 4.2

1. ለአቱሞ የመንፈስ ጭንቀት ምክንያቱ ምን ነበር?
2. የአቱሞን ማህበራዊ ህይወት በአዎንታዊ መልኩ የቀየሩትን ነገሮች መጥቀስ ትችላለችሁ?

የጤናማና ማህበራዊ ህይወት ምልክቶች የምንላቸው ፡-

- ሌሎችን በአክብሮት ማስተናገድ፣
- በቤተሰብ እና ጓደኞች መካከል የመደጋገፍ ባህል ወይም ሁኔታ መኖር፣
- ቁጡ ወይም ዝምተኛ ከመሆን ይልቅ በሰከነ መንገድ ሀሳብን የመግለፅ ችሎታ መኖር፣
- በግል እና ከሌሎች ጋር የሚያሳልፉትን ጊዜያት በአግባቡ መጠቀም፣
- በማህበረሰቡ ዉስጥ ከሚኖሩ ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘትና መተሳሰር፣
- ከማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር ራስን ማላመድ፣
- በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ እራስን መሆን፣

- ጓደኝነትንና የጓደኝነት መስመሮችን መመስረት እና ማዝለቅ መቻል፣
- ተግባቦትን ለማበረታታት እና አለመግባባቶችን በቀላሉ ለመፍታት በጓደኝነት ውስጥ ድንበር ወይም ልክ ማስቀመጥ፣ እና
- በህይወት ደስተኛ መሆን።

2. የጤናማ ማህበራዊ ህይወት ባህሪያት

የማነቃቂያ ጥያቄ

*ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ያለው ሰው ዋና ዋና ባህሪያትን ዘርዝሩ?



ምስል 4.2: የጤናማ ማህበራዊ ህይወት አንዱ መገለጫ

ጤናማ ማህበራዊ ህይወት በተለያዩ ባህሪያት ሊገለጹ ይችላሉ።።እነሱም ፡-

- ከቤተሰብ እና ከጓደኞች ጋር ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር፣
- የሌሎችን ሃሳቦች መቀበል እና የራስን አመለካከት መግለጽ፣
- መተባበር እና በጋራ መስራት፣
- እርስ በእርስ በስርዓት መግባባት እና ክብር መስጠት፣
- መቻቻል መኖር፣
- የግጭት አለመኖር፣
- የመረዳዳት ባህል መኖር፣
- ችግሮችን በውይይት መፍታት ወዘተ ... አንዱ የጤናማ ቤተሰብ እና ማህበረሰብ ማሳያ ነው።

4.3. የጤናማ ማህበራዊ ህይወት ጠቀሜታ

የማነቃቂያ ጥያቄ

1. የጤናማ ማህበራዊ ህይወት ዋና ጠቀሜታ ምንድ ነው?

2. ጤናማ ማህበራዊ ህይወት አስፈላጊ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

ጤናማ ማህበራዊ ህይወት በአዎንታዊና በአሉታዊ መልኩ በኛ መልካምነት ላይ ይንጸባረቃል ። ጤናማ ማህበራዊ ሕይወት በጣም

ጠቃሚ በመሆኑ ሁሉም ሰው ይህ አይነት ጥሩ ሰብዕና ይኖረዉ ዘንድ ይፈልጋል፡፡

ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል፡-

• በጥሩ ጓደኞች የተከበቡ እና መልካም ማህበራዊ ህይወት ያላቸው ሰዎች የተሻለ የባለቤትነት እና የአብሮነት ስሜት ይኖራቸዋል

• ላንተ የሚያስቡልህ ፣ በደስታና በሀዘንህ ወቅት ከጎንህ የሚሆኑ ሰዎች ሲኖሩህ የመንፈስ ጭንቀትህ ይቀንሳል፣

• ጤናማ ማህበራዊ ህይወት አስተሳሰባችን እንዲያድግ ያደርጋል ፤ ይጨምራል እንዲሁም ዕድሜያችንን ሊያራዝም ይችላል፣

• ሰዎች በስምምነት አብረው እንዲኖሩ ይረዳል፣

• የግለሰቦችን አካላዊ ደህንነት ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት ያሻሽላል፣

• በአጠቃላይ ጤናማ ማህበራዊ ህይወት የህብረተሰቡን ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ያሻሽላል።

4.4. በጤናማ ማህበራዊ ሕይወት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች

የማነቃቂያ ጥያቄ

በጤናማ ማህበራዊ ህይወት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶችን ዘርዝሩ?

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ጤናማ ማህበራዊ ህይወት የአጭር እና የረጅም ጊዜ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ የሚከተሉት በጤናማ ማህበራዊ ሕይወታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አንዳንድ ምክንያቶች ናቸው። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- አድሎ ማግለል እና ጭፍን ጥላቻ፣
- የወላጅ እና የልጅ ግንኙነት ብቃት/ሁኔታ፣
- አሉታዊ የወላጅ አያያዝ እና አስተዳደግ ልምዶች፣
- የግልጽነት ባህል አለመኖር።
- በመለያየት ወይም በፍቺ ምክንያት የቤተሰብ መፈራረስ እና በነጠላ ወላጅ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች መብዛት፣
- የሥራ አጥነት መጨመር፣
- የወላጅ ቸልተኝነትና ትንኮሳ፣
- የወንጀል መኖር እና ወዘተ

ናቸው።።



ምስል 4.3:- ጤናማ ያልሆነ ማህበራዊ ህይወት

ተግባር 4.3

ሶስት ተማሪዎችን የያዘ ቡድን ይመሰርቱ እና በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ

1. **በቤተሰብ ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች እና መንገዶች በመወያየት ግለፁ?**
2. **ግልጽነት አለመኖር በማህበራዊ ህይወት ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል? አስረዱ።**
3. **በመለያየት ወይም በፍቺ ምክንያት የቤተሰብ መፈራረስ አለ ብላችሁ ታስባላችሁ? አሉታዊ ውጤቶች ተወያዩበት።**
4. **አድልዎ እና ጭፍን ጥላቻ ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራሉ?**

የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቱን ለማርካት ሲል አብሮ የሚኖር ማህበራዊ ፍጡር ነው።

በመሆኑም እርስ በራሳቸዉ መልካም ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል። የጤነኛ ማህበራዊ ሕይወት አንዳንድ መገለጫ በህሪያት ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት እና ከጓደኞች ጋራ ጠናካራ ግንኙነት መፍጠር ፣ የሌሎችን ሃሳቦች መቀበል፣ ከሌሎች ጋር መተባበር፣ መቻቻልን ማሳየት፣ መረዳዳት ፣ እና ችግሮችን በዉይይት መፍታት ናቸዉ። ጤናማ ማህበራዊ ግንኙነቶች በሰዎች አካላዊ ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት ላይ የራሳቸው ተፅእኖዎች አላቸው። በመሆኑም ጤናማ ማህበራዊ ህይወት የግለሰቦችን ህይወት ያሻሽላል። በጤናማ ማህበራዊ ሕይወት

ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ነገሮች መካከል አንዳንዶቹ አድልዎና ማግለል ፣ የመቻቻል አለመኖር ፣ የግልፅነት አለመኖር እና ትንኮሳ የመሳሰሉት ናቸዉ።

ቁልፍ ቃላት

ቁጡ ወይ ግልፍተኛ፡ በቁርጠኝነት አንድን ነገር በኃይል ወይም በእልህ ማድረግ ወይም መሰል ባህሪይ ማሳየት፣

ድብርት ወይም ድባቴ፡- የመንፈስ ጭንቀት፡ የተለመደና ከባድ ሕመም ነው።

በሚሰማዎት ስሜት፣ በሚያስቡበት እና በሚያደርጉት እርምጃ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል።

ክብር፡- በሰብዓዊ ማንነታችን ከሌሎች የሚሰጠን ዋጋ፣ ቦታ ወይም እውቅና

ደካማ፡- ያለ ንቁ ምላሽ ወይም ተቃውሞ የሚሆነውን ወይም ሌሎች የሚያደርጉትን መቀበል ወይም መፍቀድ፣

ጭፍን ጥላቻ፡- “በእውነተኛ ልምድ ያልተመሰረተና ለአንድ ሰው ያለ ስሜት፣ ጥሩ ወይም ጥሩ ያልሆነ ነገር

ማህበራዊ ሕይወት፡-ከሌሎች ጋር ያሉን የተለያዩ ግንኙነቶች, እንደ ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ የማህበረሰባቸው አባላት እና እንግዶች።።

የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ መልመጃዎች

ቀጥሎ የቀረቡ የምዕራፍ ማጠቃለያ ጥያቄዎችን ስሩ፡፡

ክፍል አንድ፡ ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እዉነት ፤ ስህተት ከሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ።

1. ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ሰዎች ከሌሎች ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነት መመስረትን ይገልፃል።
2. ሰዎች ጤናማ ሕይወት ለመኖር ሲሉ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚገናኙ ማህበራዊ ፍጡራን ናቸው።
3. በማህበራዊ ህይወት እና በግለሰብ አካላዊ ደህንነት መካከል ምንም ግንኙነት የለም፡፡
4. ከጓደኞችህ ጋር ጠንካራ ግንኙነቶችን መገንባት የማህበራዊ ህይወት ደረጃን ሊያሻሽል ይችላል፡፡
5. ጤናማ ማህበራዊ ህይወት ሁሉም ሰው ሊኖረው የሚገባው መልካም የስብዕና ባህሪ ነው።

ክፍል ሁለት፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡ አማራጮች ዉስጥ ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ የቤተሰብን ጤናማ ማህበራዊ ህይወት የሚገልጸው የትኛው ነው?

   ሀ. መከባበር

   ለ. ራስን ማግለል

   ሐ. አለመግባባት

   መ. ችግሮችን በሃይል መፍታት

2. ከሚከተሉት ውስጥ የማህበራዊ ጤናማ የመሆን አመልካች የትኛው ነው?

ሀ. ጠብ አጫሪ መሆን

ለ. ሌሎችን በአክብሮት

ሐ. ቸልተኛ መሆን

መ. ጥላቻን ማስተናገድ

3. ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ በጤናማ ማህበራዊ ህይወታችን ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የማያሳድረዉ የቱ ነው?

ሀ. አድልዎ/ማግለል

ለ. ቸልተኝነት

ሐ. ሥራ አጥነት

መ. አክብሮት ማሳየት

4. ስለ ጤናማ ማህበራዊ ህይወት አስፈላጊነት ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው እውነት ነው?

ሀ. የጭንቀት ደረጃ መጨመር

ለ. ለሌሎች አሉታዊ ስሜት

ሐ. የመደጋገፍ ባህልን ማጎልበት

መ. ሰዎች አብረው እንዲኖሩ አለማበረታት

<u>ክፍል ሶስት፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ</u>

1. የጤናማ ማህበራዊ ህይወት አስፈላጊነትን ግለጹ?

2. የጤናማ ማህበራዊ ህይወት አንዳንድ ባህሪያትን ዘርዝሩ?

3. ጤናማ ማህበራዊ ህይወትን ሊጎዱ የሚችሉ አንዳንድ ምክንያቶችን አብራሩ?

ምዕራፍ አምስት

ትብብር እና በጋራ መስራት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፡-

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረዉ ሲያጠናቅቁ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡

- **ትብብር እና የቡድን ስራን ማብራራት፣**
- **በማህበረሰባቸዉ እና በትምህርት ቤታቸዉ ውስጥ የመተባበር እና የቡድን ስራ ባህልን ትለያላችሁ፡፡**
- **የትብብር እና የቡድን ስራ መርሆዎችን ታደንቃላችሁ**
- **የትብብር እና የቡድን ስራ ክህሎቶችን ታንጸባርቃላችሁ፣**
- **የትብብር እና የቡድን ስራን ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ።**

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በዋናነት በትብብር እና በቡድን ስራ ጽንሰ ሀሳብ ላይ ያተኩራል፡፡ በተለይም በየማህበረሰባችን በሚገኙ የመተባበር እና የቡድን ስራ ባህሎች እንደ ደቦ ወይም ጂጊ፣ እድር፣እቁብ እና የትምህርት ቤት ቡድን ስራን በሚመለከት ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም የትብብር እና የቡድን ስራ መርሆችን ይዘረዝራል። በተጨማሪም በተመረጡ የትብብር እና በጋራ መስራት የቡድን ሥራ ዓይነቶች ፤ በተለይም በጎ አስተሳሰብ ፣ ተግባቦት ፣ መደራጀት ፣ ክርክር፣ እና የጊዜ አጠቃቀም ክህሎቶች በግልፅ ያስረዳችኋል፡፡

በመጨረሻም ምዕራፉ የመተባበር እና በጋራ መስራት የቡድን ስራን ጠቀሜታ አጉልቶ ያሳያል።

5.1 መተባበር እና በጋራ መስራት

የማነቃቂያ ጥያቄ

* በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቡድን አላችሁ?

ሰዎች የጋራ ግብን ለማሳካት አብሮ በጋራ የመስራት ሂደት የትብብር እና የአብሮነትን ፅንሰ-ሀሳብ ሊያስረዳን ይችላል። በጋራ መስራት እና ትብብር በተናጥል ለማከናወን አስቸጋሪ የሆኑትን ተግባራት ቀላል ያደርጋሉ። በመሆኑም እነዚህ እሴቶች ሰዎች ተግባራቸውን በብቃትና በውጤታማነት እንዲያከናውኑ ይረዳሉ።

ትብብር እና በጋራ መስራት የሚከተሉት ሃሳቦች ያስፈልጉታል፡

- ቡድኑን ለመርዳት ብዙ የሚተጉ ሰዎች መኖር፣
- በቡድን አባላት መካከል የወዳጅነት ስሜት፣
- የቡድን መሪዎች ወይም አስተባባሪዎች፣
- የጋራ ፍላጎት ወይም ግብ ናቸው።

ተግባር 5.1

1. የመተባበር እና የጋራ ስራ ተዋኒያንን ጥቀሱ?
2. አንድን ስራ በተናጠል እና በቡድን የመስራት ጥቅሞችን አብራሩ?

5.2. የመተባበር እና በጋራ የመስራት ባህል በማህበረሰብ እና በትምህርት ቤት

የማነቃቂያ ጥያቄ

*** በማህበረሰባችሁ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ቡድኖችን መጥቀስ ትችላላችሁ?**

_____

5.2.1. በማህበረሰቡ ውስጥ፡-

ኢትዮጵያውያን በበርካታ ቡድኖች እና በመተባበር ስሜት አብረው የመስራት ረጅም ታሪክ አላቸው። እነዚህ ቡድኖች በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የራሳቸው ስያሜዎች እና ሂደቶች አሏቸው፡፡ ሰዎች እነዚህን የጋራ ባህላዊ ተቋማት ለተለያዩ ዓላማዎች ይጠቀማሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

1. **ደቦ (ጂጊ)**

   በበርካታ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሰዎች የተለያዩ ስራዎች በጋራ ለመከወን የሚያሳዩት የቡድን ስራ ነው። በእርሻና በምርት መሰብሰቢያ ወቅት በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ተጠራርተዉ በጋራ ይሠራሉ፡፡ እንደህ አይነቱ ሀገር በቀል ልምድ በመላ አገሪቱ በጣም የተለመደ ነው። ደቦ ወይም ጂጊ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፣ ለምሰሌ በግለሰቦች መካከል ወዳጅነትን ያጠናክራል፣ የመደጋገፍ ባህልን ያዳብራል፣ እና ሰፋ ያለ ስራን በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ይህ እሴት በማህበረሰቡ ዉስጥ የሚኖሩና የተለያዩ ተግባራትን መከወን የማይችሉ አቅመ-ደካማ ግለሰቦችን ለመደገፍ ያለመ ነው፡፡



ምስል.5.1. ደቦ/ጂጊ በማህበረሰቡ ውስጥ

2. **እድር፡-**

በጎረቤት እና በተመሳሳይ ስራ ቦታ የሚገኙ ሰዎች ሞትና የመሳሰሉት ድንገተኛ አጋጣሚዎችን ሲከሰቱ የሚጠቀሙትን ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚመሠረት ማህበር ነው፡፡ በሚገባ የተደራጀና በተመሳሳይ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ህብረት ነው። በአባላቱ በተመረጡ መሪዎች አማካይነት ጥብቅ ሂደቶችን የሚከተል ማህበራዊ ተቋም ነዉ፡፡

5.2.2. በትምህርት ቤት ውስጥ በጋራ መስራት

የቡድን ወይም የጋራ ስራ ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ በመረዳዳት የመማር ዘዴን ወይም ሂደትን ያመለክታል። ይህ ክህሎት ተማሪዎች አብረው በመሆን ተግባራትን የሚከውኑበት ሂደት ነው። ተማሪዎች እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸዉን እና ልምዶቻቸውን እንዲያካፍሉ

ይረዳቸዋል። እያንዳንዱ ተማሪ ለቡድኑ ጠቃሚ የሆነ ነገር ማበርከት ይጠበቅበታል።



ምስል.5.2. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በጋራ ሲሰሩ

ተግባር 5.2

1. የመተባበርና በጋራ የመስራት ባህልን ጠቀሜታ በመወያየት ምላሻቸሁን ለመምህራችሁ ንገሩ?
2. በማህበረሰባችሁ ዉስጥ ደቦን በመሳሰሉ የጋራ ሰራዎች ያላችሁን ልምድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ?
3. አካባቢያችሁ ውስጥ ያሉ እንደ ደቦ ዓይነት በጋራ የመስራት ዘዴዎችን ጥቀሱ

5.3. የመተባበር እና በጋራ የመስራት መርሆዎች

የማነቃቂያ ጥያቄ

የቡድናችሁን አባላት ስም መጥቀስ ትችላላችሁ?

ትብብር እና የበቡድን መስራት ተለይተው የሚታወቁ መርሆዎች አሏቸው። የቡድን ዓባላት ስለ ጋራ ስኬታቸዉ ሲባል ሊከተሏቸዉ የሚገቡ የተለያዩ መርሆዎች አሉ፡፡ እነሱም ፡-

1. አዎንታዊ መደጋገፍ፡-

ሁሉም አባላት በተናጠል ከመስራት ይልቅ በጋራ የመስራት አስፈላጊነትን ማመን አለባቸው፡፡

2. የተናጠል ኃላፊነት፡

በቡድን ውስጥ እያንዳንዱ ዓባል ግለሰብ የሚጠበቅበትን ለቡድኑ መከወን አለበት።

3. የቡድን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ፡

የጋራ ስራ ዉጤት የእያንዳንዱ ዓባል አስተዋፅኦ ነው።

4. የተግባቦት ክህሎት ፡-

ተግባቦት የጋራ ስራ ስኬት ቁልፍ መሳሪያ ነዉ፡፡ ይህ የመግባባት ችሎታ በቡድን በአባላት መካከል መተማመንን ከመፍጠር ባሻገር በሚሰሯቸዉ ተግባራት ዙሪያ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ይረዳቸዋል፡፡

5. የሚያበረታታ መስተጋብር፡

የጋራ ግብ ላይ ለመድረስ አባላት የሌሎችን ጥረት መረዳት፣ ማበረታታት እና መደገፍ አለባቸው፡፡

ተግባር 5.3

1. ስለ መተባበር መርሆዎች በየቡድናችሁ ተወያዩ?
2. የጋራ ስራ ልምዳችሁን እና እያንዳንዱ አባል ለቡድኑ ውጤታማነት ያለውን አስተዋፅኦ እንዴት እንደሚያደርግ ለክፍል ጓደኞችዎ አካፍሉ?

5.4. የመተባበር እና የጋራ ስራ ብቃቶች

5.4.1 የሀሳብ ብዝሃነትን ማስተናገድ

የማነቃቂያ ጥያቄ

በቡድናችሁ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሀሳብ ለማዳመጥ ፈቃደኛ ናችሁ?

ብዝሃ-ሀሳብን ማስተናገድ ማለት የሌሎችን ሃሳቦች እና መረጃዎች የማድመጥ ፈቃደኛነት ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ይህን ስንል በቡድኑ ውስጥ ሊቃወሙን የሚችሉ ሰዎችን ማዳመጥንም ይጨምራል። በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ሌሎችን የማሳመን ችሎታንም ያካትታል። በፈቃደኝነት እውነትን ፈልጎ የቡድን ዓባላትን ትብብር እና ብቃትን የማጠንከር ክህሎት ጭምር ነዉ።

ብዝሃ-ሀሳብን ማስተናገድ ቡድኑን በሚመለከት ግልጽ ባልሆኑ እቅዶች፣ አስተያየቶች ላይ፣ ግቦች እና እንቅስቃሴዎች ጥያቄዎችን መጠየቅን ያካትታል። በቡድን ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንድንሆን ያግዘናል። በመሆኑም ይህ ችሎታ የመቀበልም የመከላከልም ጉዳይ ሆኖ የቡድን ዓባላት በመተጋገዝ መንፈስ ተግባራትን እንዲፈፅሙ ያስችላቸዋል።

ተግባር 5.4

1. ስለ ብዝሃ-ሀሳብ ማስተናገድ ብቃት ከቡድን ዓባላት ጋር ተወያዩ?
2. ሃሳባችሁን በግልፅ ማብራራት ትችላላችሁ? ወይም የሌሎችን ለማዳመጥ ፈቃደኛ ናችሁ? ያላችሁን ልምድ በክፍል ውስጥ አካፍሉ?

5.4.2. ተግባቦት

የማነቃቂያ ጥያቄ

ለጓደኞቻችሁ መረጃን የምትሰጡበት እና የምትቀበሉበት ዘዴ ምንድነው?





ምስል5.3. ሰዎች በተለያዩ ጉዳዮች ግንኙነት ሲፈጥሩ

ተግባቦት መረጃን የመስጠት፣ የመቀበል እና ለሌላዉ ለማድረስ ከሰዎች ጋር የምናደርገዉ የግንኙነት ተግባር ነው። በመሆኑም ንግግርን፣ ጽሁፍን፣ እና መረጃ ማድመጥን ወይም ማንበብን ያካትታል። በቀላል አገላለፅ መረጃን ከአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ወደ ሌላዉ ማስተላለፍ

ነዉ:: ተግባቦት በተለያየ መንገድ ሊከወን ይችላል ይኸውም በድምፃዊ ንግግርና በድምፅ አልባ ንግግር ዘዴዎችን ሊጨምር ይችላል፡፡
በተጨማሪም ተግባቦት የቡድን ዓባላት የጋራ ዓላማቸዉን ያሳኩ ዘንደ በዉስጣቸው አንድ ዓይነት መረዳትን የሚያሳድግ ክህሎት ነው፡፡ ውጤታማ ተግባቦት በጥሞና ማድመጥን፣ በግልፅ መናገርን እና የተሳታፊዎችን ብዘሃ ዕይታን ማክበርን ይጠይቃል፡፡

ተግባር 5.5

1. የተግባቦት ጽንሰ-ሐሳብ ምንነት ላይ ተወያዩ?
2. በቡድን ውይይት ወቅት የሚያጋጥማችሁን የተግባቦት ተግዳሮቶች ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ?

5.4.3. መደራጀት

የማነቃቂያ ጥያቄ

ድርጅት የሚለውን ቃል ስትሰሙ ወዲያው ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣው ምንድን ነው?

መደራጀት የጋራ አላማ ያላቸው ሰዎች አንድን ተግባር ለመፈጸም የሚፈጥሩት ስብስብ ወይም ህብረት ነው፡፡ የመደራጀት አስፈላጊነት የሚመነጨው ብዙ ሰዎች ለተመሳሳይ ዓላማ በጋራ መስራታቸው አንድ ግለሰብ በተናጠል ከሚሠራው እጅግ ውጤታማ በመሆኑ ነው፡፡ ድርጅት ሀሳቦች፣ ክስተቶች፣ ማስረጃዎች እና ሀብቶች ማዘጋጅት ማሟላት ይኖርበታል፡፡ ይህን ለማሳካት በጋራ መስራት ያስፈልጋል፡፡



ምስል.5.4. በአንድ ድርጅት ውስጥ አባላቱ በጋራ ሲሰሩ

ተግባር. 5.6

1. **መደራጀት ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በቡድን በመሆን ተወያዩ**
2. **በየቡድናችሁ የመኪና ሞዴል ለመስራት የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች አደራጁ?**

5.4.6. ክርክር

የማነቃቂያ ጥያቄ

*** ክርክር ማለት ምን ማለት ነው?**

ክርክር ስንል አንድን ጉዳይ አስመልክቶ አንዱ ልላኛዉን ለማሳመን የሚደረግ የሀሳብ ሙግት ማለት ነዉ። ተከራካሪዎች በውይይቱ ርዕስ ዙሪያ የታዳሚውንና የተቀናቃኛቸውን ስሜት ለማሸነፍ እና ቀልብ ለመግዛት የሚሞክሩበት ዘዴ ነው።



ምስል.5.5. በቡድኖች መካከል ክርክር ሲደረግ

የክርክር አላማ ለተቃራኒ ቡድን የራስን ሀሳብ ትክክል እንደሆነ ማሳመን መቻል ነው ። ክርክር በዳኞች የድምፅ ውሳኔ ወይ በተከራካሪዎች መካከል በሚፈጠር ስምምነት ያበቃል። ክርክር ተከራካሪዎች ሊያከብሯቸዉ የሚገባቸው ጥብቅ መተዳደሪያ ህግ ወይም ህገ-ደንብ ይኖረዋል።

ክርክር ለትብር በትብብርና በቡድን ሥራ አስፈላጊ ክህሎት ነዉ። ይህ ክህሎት በቡድን ዓባላት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ሁኔታዎችን ለመፍታትና መስመር ለማስያዝ ይረዳል። እንዲሁም በቡድን ውስጥ ብኽኮታና ግራ መጋባት ሲከሰት ለማጥራት ያግዛል።

ተግባር 5.7

1. ስለ ክርክር ጽንሰ-ሐሳብ በቡድን በመሆን ተወያዩ?

2. መምህራችሁ በሚያደራጀዉ ቡድን አማካኝነት አንድ ርዕስ ምረጡ እና በክፍል ውስጥ ተከራከሩበት?

5.4.7. የጊዜ አጠቃቀም

የማነቃቂያ ጥያቄ

በየቤታችሁ የምትጠቀሙትን የጥናት መርሃ ግብር መንገር ትችላላችሁ?

የጊዜ አጠቃቀም ያለንን ጊዜ ለተለያዩ ተግባራት ለማብቃቃት እና የምናቅድበት ሂደት ነው። የምናከናውናቸዉን ተግባራት እንደሁኔታዉ በቅደም-ተከል እንድንፈፅም ይረዳናል። ጊዜያችንን በአግባቡ ስንጠቀም ስራዎቻችንን ባለን ጊዜ ማጠናቀቅ እንቻለን። ጥሩ የጊዜ አጠቃቀም ስራዎችን በቅልጥፍና እና በብልህነት እንድንከዉን ያስችለናል።

ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም የሚከተሉትን ሂደቶች ይፈልጋል፡-

- **ሊደረስባቸው የሚገቡ ግቦችን ማስቀመጥ፣**
- **በአስፈላጊነታቸው መሰረት ተግባራትን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣**
- **እያንዳንዱ ተግባር የሚከወንበትን እቅድ ወይም የጊዜ መርሐግብር ማዘጋጀት፣**
- **ማቀድ፣**
- **በእቅዳችሁ መሰረት ተግባራትን ማከናወን ።**



ምስል.5.6. የጊዜ አጠቃቀም ያሳያል

ተግባር 5.8

1. በየቡድናችሁ ስለ ጊዜ አጠቃቀም ጽንሰ-ሀሳብ ተወያዩ?

2. በየቤታችሁ ውስጥ የምታከናዉኑትን ተግባራት በመዘርዘር እና ለእያንዳንዱ ተግባር ተገቢውን ጊዜ በመመደብ ዝርዝራችሁን ለክፍል ጓደኞች አካፍሉ

5.4.8. የመተባበር እና የጋራ ስራ አስፈላጊነት/ጠቀሜታ

የማነቃቂያ ጥያቄ

የመተባበር እና የጋራ ስራ ጽንሰ-ሀሳቦችን ምንነት አብራራ/ሪ

ትብብር እና የጋራ ስራ በጣም ጠቃሚ የሕይወት ክህሎቶች ናቸው። እነዚህ ብቃቶች ሰዎች ልምዶቻቸውን ልምዳቸውን፣ እውቀታቸውን

እውቀታቸውን፣ ክህሎቶቻቸውንና ክህሎታቸውንና አቅማቸዉን ለቡድን አባላት እንዲያካፍሉ ይረዳሉ፡፡ የተለያዩ ልምድ ያላቸዉ ሰዎች በጋራ እንዲሰሩ እና እርስ በርስ እንዲረዳዱ ያበረታታል፡፡ በተጨማሪም የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ለመፍታት እና የጋራ ግቦችን ለማሳካት አዳዲስ ሃሳቦችን ይጠቁማሉ፡፡

በትምህርት ቤት ውስጥም ተባብሮ መስራት የተማሪዎችን በራስ መተማመንና ለራስ የሚሰጥን ዋጋን ለማዳበር ይረዳል፡፡ የአቻ ግንኙነቶችን እና ተግባቦትን ያበረታታ ያሳድጋል፤የአቻ ግንኙነቶችን ያጠናክራል ፤ትብብር ነገሮችን የማደረጀት ስራን ቀላል ያደርጋል፡፡



ምስል.5.7. የትብብር እና የቡድን ስራ አስፈላጊነት

ተግባር 5.9

1. ስለ ትብብር እና የጋራ ስራ አስፈላጊነት በቡድን በመሆን ተወያዩ?

2. የክፍል ስራን በግል መስራት ወይስ በቡድን መስራት ይሻላችኋል? የራሳችሁን ተሞክሮ ለክፍል ጓደኞች ስለማጋራትስ እንዴት *ታያላችሁ?*

የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ

ሰዎች በመሰባሰብ የጋራ ዓላማን ለማሳካት የሚሰሩበትን ሂደት ትብብር እና የጋራ ስራ ብለን መዉሰድ እንችላለን፡፡ ይህ ክህሎት በተናጠል ለመስራት የሚከብዱ ተግባራትን በጣም ቀላል ያደርጋል፡፡ ኢትዮጵያውያን በትብብር መንፈስ አብሮ የመስራት የረጅም ጊዜ ታሪክ አላቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል ደቦ (ጂጊ) እና እድር ጥቂቶቹ ናቸው።

ዉጤታማ አብሮነት ይኖር ዘንድ ትብብር እና የጋራ ስራ ተለይተው የሚታወቁ መርሆዎች አሉዋቸው፡፡ ብዝሃ ሃሳብን ማስተናገድ፣ ተግባቦት፣ አደረጃጀት፣ የመላመድ ብቃት፣ ክርክር፣ የጊዜ አያያዝ እና ችግርን የመፍታት ችሎታዎች ለስኬታማ ትብብርና የቡድን ስራ ከሚያስፈልጉ ብቃቶች ዉስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ሁሉም ሰውዉ ያለውን ዕዉቀት፣ አቅም እና ክህሎት ለቡድኑ ስለሚያበረክት ትብብር እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነዉ፡፡

ቁልፍ ቃላት

መተባበር፡- አንዱ ከሌላ ሰው ወይም ቡድን ጋር አንድን ነገር ለማሳካት ወይም ለመፈፀም መስራት፡፡

መስተጋብር፡- የጋራ ወይም የሰጥቶ መቀበል ሂደት የጋራ አላማ ያላቸው ሰዎች አንድን ተግባር ለመፈጸም የሚፈጥሩት ስብስብ ወይም ህብረት ነው፡፡

ክርክር፡- የሀሳብ ሙግት

የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ክፍል አንድ፡ የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እዉነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. ትብብር እና የቡድን ስራ በተናጠል ለመስራት ለሚያዳግቱ ተግባራት የበለጠ ተስማሚ ናቸው፡፡
2. ተግባቦት ለተቀባዩ መረጃ የመስጠት ተግባር ብቻ ነው።
3. ብዘሃ ሃሳብን ማስተናገድ የሌሎችን ሃሳብ ለመቀበል ፈቃደኛ የመሆን ችሎታን ያካትታል፡፡
4. ክርክር ተከራካሪዎቹ ሊከተሏቸው የሚገቡ ጥብቅ የስነምግባር ህጎች አሉት።

ክፍል ሁለት፡- በ "ሀ" ስር የቀረቡትን የትብብር እና ቡድን ስራ ክህሎቶች በ "ለ" ስር ዉስጥ ከተቀመጡ ትርጉማቸዉ ጋር አዛምዱ፡፡

አምድ 'ሀ'	**አምድ 'ለ'**
1. ከአዲስ ነገሮች ጋር የመጣጣም ችሎታ	ሀ/ ክርክር
2. የሀሳብ ሙግት	ለ/
3. የመረጃ ልውውጥ	ሐ / መደራጀት
4. በተወሰነ ጉዳይ ላይ መደበኛ ውይይት ማድረግ	መ/ ተግባቦት

ክፍል ሦስት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጡ፡፡

1. ገንዘብ ለአደጋ ጊዜ ለማሰባሰብ በጎረቤቶች መካከል የሚመሠረት ማህበር የትኛው ነው?
   - ሀ. ደቦ
   - ለ. እቁብ
   - ሐ. እድር.
   - መ. ጂጊ
2. ከሚከተሉት ውስጥ የጋራ ሥራ መርህ ያልሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ. አዎንታዊ መደጋገፍ
   - ለ. ሌሎቹን መጉዳት
   - ሐ. የተናጠል ኃላፊነት
   - መ. የተግባቦት ክህሎት

3. ከሚከተሉት ዉስጥ መፍትሔ የማፈላለግ ተግባር የትኛው ነው?

ሀ. የጊዜ አጠቃቀም

ለ. ሂሳዊ አስተሳሰብ

ሐ. ችግር መፍታት

መ. ብዘሃ ሃሳብን ማስተናገድ

ክፍል አራት፡ ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎቹ አጫጭር መልሶችን ስጡ

1. የትብብር እና የጋራ ስራ ጠቀሜታን ግለጽ/ጪ/ ጥቀሱ?
2. ስኬታማ የጊዜ አጠቃቀም ሂደቶች ምን ምን ናቸው?
3. ችግር በሚፈታበት ጊዜ ልንከተላቸው የሚገቡ እርምጃዎችን አብራሩ?

ምዕራፍ ስድስት

የባህል ብዝሃነት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፡-

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ ፡-

- **የባህል ብዝሃነትን ትርጉም ታብራራላችሁ፤**
- **የባህል ብዝሃነትን ማስተናገድ ያለውን ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ፤**
- **የማህበረሰባችሁን ባህል ብዝሃነትን ታደንቃላችሁ፤**

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የባህል ብዝሃነትን ትርጉም ያስተዋውቃችኋል። እንዲሁም የባህል ብዝሃነትን የማስተናገድ አስፈላጊነትና ጠቀሜታን በሚመለከት ግንዛቤን ይፈጥርላችኋል፡፡ የባህል ብዝሃነት መሠረታዊ መገለጫ የሆኑትን እንደ ብሄረሰብ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ የአለባበስ ዘይቤዎች፣ ባህላዊ ሙዚቃዎች፣ ባህላዊ ምግቦች እና ባህላዊ የሰርግ ስርአቶችን በስፋት ይመለከታል፡፡

በስተመጨረሻም የባህል ብዝሃነትን የማስተናገድ ጥቅሞችና መንገዶችን ያብራራል፡፡

6.1. የባህል ብዝሃነት ትርጉም

የማነቃቂያ ተግባር

*** የብዝሃነትን ትርጉም አብራሩ?**

*** ስለ ባህላዊ ብዝሃነት መሰረቶች ተወያዩ?**

"ብዝሃነት" በጥቅሉ ሲታይ በሰዎች መካከል ያለ ልዩነት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ይህም በሰዎች መካከል የሚታዩ እና የማይታዩ ልዩነቶችን የሚያካትት ሆኖ በግለሰብ እና በቡድን ደረጃ ሊመዘን ይችላል። በሌላ በኩል ብዝሃነት በአንድ ቡድን ዉስጥ እና በተለያዩ ቡድኖች መከካል ፣ ብሄርን፣ ቋንቋን፣ ኃይማኖትን፣ ያታን እና የኑሮ ደረጃን መሠረት በማድረግ ያሉ ልዩነቶች ናቸው ።

የባህል፣ የሃሳብ፣ የዕይታ እና የዕምነት ብዝሃነቶች የተሻለ ማህበረሰብ የመፍጠር ራዕያችንን ያዳብራሉ። የተለያዩ ባህሎች የተሻለ ህይወትን በሚመለከት የተለያዩ የትርጓሜ ሥርዓቶች፣ እሴቶች እና ጽንሰ-ሀሳቦችን ያጎናፅፉናል። ይህ መሆኑ ደግሞ ስለ ዓለም ያለንን ግንዛቤ ያሰፋሉ።

በዚህም ምክንያት የባህል ብዝሃነት ፍላጎታችንና ምርጫችንን ለማብዛት እንደ ጠቃሚ ምንጭ ተደርጎ ይወሰዳል። በተጨማሪም የባህል ብዝሃነት የሕይወት ራዕያችንን ጥልቀት እንዲኖረዉ ከማድረጉም ባሻገር የማህበራዊ ሕይወት እይታችንና ስለራሳችን ያለንን ግንዛቤ በሚገባ ያዳብርልናል። የሃሳብ ልዩነቶች መኖር የኑሮ ዘይቤ አማራጭ የታሪክ አረዳድ እንዲኖረን በማድረግ አዎንታዊ የአለም ዕይታ እንዲኖረን ያግዘናል።



ምስል 6.1፡ ብዝሃነት በኢትዮጲያ

6.2. በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የባህል ብዝሃነት ዓይነቶች

ባህል ማለት የማንኛውም ማህበረሰብ አካል የሆኑ ምልክቶች፣ ቋንቋዎች፣ እምነቶች፣ እሴቶች፣ እና ቅርሶችን የሚያካትት ፅንሰ-ሀሳብ ነው። ባህል እና ማህበረሰብ የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ባህል ያለማህበረሰብ እና ማህበረሰብ ያለ ባህል አይኖሩም፡፡ በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ ማህበረሰብ ከሌላዉ የሚለይበት የራሱ የሆነ ባሕል አለው፡፡ የባህል ብዝሃነትም ከዚህ ሃቅ የሚመነጭ ነዉ፡፡ የባህልን ብዝሃነት የሚያሳዩ ዋና ዋና ሰበዞች፡- በሄር ብሄር ፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ባህላዊ አለባበስ፣ ባህላዊ ሙዚቃ፣ ባህላዊ ምግብ፣ የሰርግ ስርዓትና የመሳሰሉት ናቸዉ ናቸው፡፡

6.2.1. ብሄር

ብሄር ሲባል የጋራ የሆነ ባህላዊ ልምዶችና እሴቶች ያሉት የሰዎች ማህበራዊ ስብስብ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ብሄር በቋንቋ፣ በታሪክ፣ በባህል፣ በኃይማኖትና በማህበራዊ ስነ-ልቦና የጋራ ማንነት ያላቸው

ሰዎች ወይም ቡድኖች በሚኖሩበት አካባቢ የሚፈጠር ስብሰብ ነዉ፡፡በመሆኑም ብሄር ውስጣዊ ትስስር እና የዝምድና እና የአካታችነትን ስሜት ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ብሄር የባህል ልዩነት መሰረት ተደርጎ ይቆጠራል።

6.2.2. ባህላዊ አልባሳት

ባህላዊ አልባሳት የጌጣጌጦችና መሰል ቁሶች ስብስብ ሆኖ ከጥንት ጀምሮ ለረጅም ጊዜ ተለይቶ በታወቁ ሰዎች የሚለበስ ልብስ ነዉ፡፡ አልባሳት በዕለተ ተዕለት ሕይወታችን አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ፍላጎቶች ናቸዉ፡፡ ሰዎች በአለባበሳቸዉ ማንነታቸዉን ከመግለፅ አልፈው በማህበረሰብ ዉስጥ ያላቸዉን ደረጃ ያሳዩበታል፡፡ የሀገራችን ኢትዮጵያ ህዝቦች በተለያዩ አካባቢዎች የራሳቸዉ የአለባበስ ስርዓት ያላቸዉ ሲሆን የብዝሃነታችንም አንዱ መገለጫ ሆኖ ይታያል፡፡



ምስል 6.3፡ የኢትዮጵያ የባህል አልባሳት አብነቶች

6.2.3. ባህላዊ ሙዚቃ

ሙዚቃ ከባህላዊ ማንነታችን ጋር የተቆራኘ ነው። እኛነታችንን እንድንገልፅና የጋራ ማንነታችንን እንድንፈጥር ይረዳናል። የተወሰኑ መመሳሰሎች ቢኖሩትም የባህል ሙዚቃ እንደየባህሉ ይለያያል። የባህል ሙዚቃ አንዱ ባህላችንን የምንገልፅበት መንገድ በመሆኑ እጅግ ጠቃሚ ነው ። በተጨማሪም የባህላዊ ሙዚቃ ጠቀሜታ ሰዎች እርስ በእርስ እንዲገናኙና ማንነታቸዉን ፈልገዉ እንዲያገኙ መርዳቱ ነው። በተጨማሪም የባህል ሙዚቃ ሰዎች ቋንቋን እንዲማሩ ያግዛቸዋል።



ምስል 6.4፡ የኢትዮጵያ የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች

6.2.4. ባህላዊ ምግብ

ባህላዊ ምግብ ሲባል ምግብን የመሥራት፣ የመብላት፣ እና የአቀራረብ ዘዴዎችን እና ሂደቶችን ያካትታል። ኢትዮጵያውያን ባህላዊ ቅርሶቻቸውንና ልማዳቸዉን በመጠበቅ የሚኮሩ ሲሆን እያንዳንዱ የአገሪቱ ክፍል የራሱ የሆኑ ባህላዊ ምግቦች አሉት። በተጨማሪም በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የሌላዉን አካባቢ ባህላዊ ምግብ

የመመገብና የማድነቅ ልምዶች አሁን አሁን በሀገራች እየተዘወተሩ መጥተዋል።



ምስል 6.5፡ የኢትዮጵያ የባህል ምግቦች በከፊል

6.2.5. ባህላዊ የሰርግ ስርአት

ሰርግ ሁለት ሰዎች በትዳር ውስጥ የሚዋሀዱበት ሥነ ሥርዓት ነው። የሠርግ ወጎች እና ልማዶች በባህሎች ብሔረሰቦች፣ ሃይማኖቶች፣ በሀገራት እና ማህበራዊ መደቦች መካከል በጣም ይለያያሉ ።

አብዛኞቹ የሠርግ ሥነ-ሥርዓቶች በጥንዶች የጋብቻ ቃል ኪዳን መለዋወጥን የስጦታ አቀራረብን (መባ ፣ ቀለበት ፣ ወካይ ቁስ ፣ አበቦች ፣ ገንዘብ፣ አልባሳት፣ የቀንድ ከብቶች) እና ጋብቻቸዉን በኃይማኖት አባት ወይም በሌሎች አማካኝነት በይፋ ማብሰርን ያካትታል። በኢትዮጵያ እና በሌሎችም የዓለም አካባቢዎች የተለያዩ የሰርግ ባህሎች ያሉ ሲሆን የብዝሃነት እነዱ መሰረት ተደርጎ ይወሰዳል።



ምስል 6.6፡ የተለያዩ የሰርግ ባህል በኢትዮጵያ

6.3. የባህል ብዝሃነትን የማስተናገድ አስፈላጊነት/ጠቀሜታ

ኢትዮጵያ የበርካታ ህዝቦች እና ባህሎች ሀገር ነች። እነዚህን እና ሌሎች ልዩነቶችን ማክበር ማስተናገድ በሰላም እና በትብብር ለመኖር እጅግ አስፈላጊ ናቸው ። የባህል ብዝሃነት መኖር ማለት የተለያዩ የአለባበስ ዘይቤዎች፣ ባህላዊ ምግቦች፣ የባህል ውዝዋዜዎች መኖር ሲሆን የእነዚህ ሁሉ መኖር ኢትዮጵያን ውብና ማራኪ ያደርጋታል። ይህም ብዙ ቱሪስቶችን በመሳብ እና የሀገራችንን ገቢ ይጨምራል።

ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ የባህል ቡድኖች አዲስ ፈጠራና ግኝቶችን ይሰጡናል። በተጨማሪም ከተለያዩ ባህል ቡድኖች የመጡ ሰዎች አዳዲስ ቋንቋ ስለሚያስተምሩ፣ ዕዉቀታቸዉንና ልምዳቸዉን ስለሚያበረከቱልን ይህ ልዩነት አገራችንን የበለጠ አስደሳች የመኖሪያ ቦታ ያደርገዋል ። የባህል ብዝሃነት ወይም ስብጥረ ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት አንስተናል። ባህሎቻችን እኩል ስናያቸው ተጠቃሚ መሆን እንችላለን። በአለባበስ ዘይቤዎች፣ ጭፈራዎች፣ ባህላዊ ምግቦች፣ ወዘተ. የሚሰተዋሉ ልዩነቶችን ልናከብር ይገባል። እነዚህን እና ሌሎች ባህላዊ

ልዩነቶችን ማክበር የምንችለዉ በባህል እኩልነት ስናምን ነዉ። መከባበር ድህነት እና ኋላቀርነት የመሳሰሉ የጋራ ጠላቶቻችንን እንድንዋጋና ሀገራችንን እንድናለማ ይረዳናል።

ተግባር 6.1 የቡድን ሥራ፡-

የባህል ልዩነትን ማስተናገድ ስላለው ጠቀሜታ በቡድን ተወያዩ?

6.4. የባህል ልዩነትን የማስተናገድ መንገዶች

የባህል ልዩነቶችን ማስተናገድ የሁሉም ባህል ቡድኖች የጋራ ህልውና ነው። ይህም ማለት የሌሎችን ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶች እና የአኗኗር ዘይቤዎች በማክበር አብሮ መኖር ማለት ነው። አስተሳሰቡ የሁሉም ባህሎች፣ ሃይማኖቶች እና ቋንቋዎች እኩል መሆናቸውን በማመን የተመሰረተ በመሆኑ ሁሉም ሰው እኩል ሊስተናገድ ይገባዋል።ማህበረሰብ በሰላም ሊኖር የሚችለዉ ሁሉም አባላቱ እርስ በእርሳቸዉ የጋራ መከባበር እስካላቸው ድረስ ብቻ ነዉ። ይህን አለማድረግ በቀላሉ ማህበራዊ ሰላምን ሊያናጋ እና እንደ አንድ ማህበረሰብ እንዳንኖር ያደርጋል።

የሚከተሉት መንገዶች የባህል ልዩነትን ለማስተናገድ የሚረዱ ናቸው።

- ለባህል ልዩነቶች እውቅና መስጠት፣
- የራስን ባህል የላቀ ወይም የበታች አድርጎ የመቁጠር ዝንባሌን ማስወገድ፣
- ልዩነቶችን ማክበር፣

- የግለሰቦችን ወይም የማህበረሰብን የአኗኗር ዘይቤዎች እንደ ጎላ ቀር ከመቁጠር መቆጠብ፣
- ሌሎች ባህሎች የሚያቀርቡትን አስተዋፅኦ ዋጋ መስጠት፣
- የሌሎችን ባህል ለማድነቅ በአስተሳሰብ ዝግጁ መሆን፣

ተግባር 6.2

1. በማህበረሰባችሁ ዉስጥ የባህል ብዝሃነትን ማስተናገድ የሚቻልባቸውን መንገዶች በቡድን ተወያዩ

የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ

ብዝሃነት በአንድ ቡድን ዉስጥ እና በተለያዩ ቡድኖች መከካል ዘርን፣ ብሄርን፣ ቋንቋን፣ ኃይማኖትን፣ ያታን እና የኑሮ ደረጃን መሠረት በማድረግ የተፈጠረ ልዩነት እንደሆነ መረዳት እንችላለን፡፡ የብዝሃነት ባህሎች ለግለሰቦች ትርጉም ያለዉ አማራጭ ያቀርባሉ፡፡ እያንዳነዱ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ባህላዊ መገለጫ ሲኖረዉ የብዘሃነትም ምንጭ ሆኖ ይታያል፡፡ ዋና ዋና የብዝሃነት ምንጮች ብሄር፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ባህላዊ አለባበስ፣ ባህላዊ ሙዚቃ፣ ባህላዊ ምግብ እና የሰርግ ስርዓትና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

በሰላም እና ትብብር ለመኖር እነዚህን እና ሌሎች ልዩነቶችን በመቻቻል ማስተናገድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በባህል ብዝሀነት ዉስጥ በሰላም መኖር የሚቻለዉ ሁሉም አባላቱ እርስ በእርሳቸው መከባበርን እስካሳዩ ድረስ ነዉ። የባህል ብዝሃነትን ማስተናገድ ለበርካታ የባህል ልዩነቶች ዕውቅና መስጠትን፤ የአንዱን ባህል ከፍ አድርጎ የሌላዉን ዝቅ

አለማድረግን ይጠይቃል፤ ልዩነቶችን ማክበር፤ እና የተለያዩ ባህላዊ አገላለያችንና አስተዋፅያችን ጠቀሜታ መገንዘብን ይፈልጋል፡፡

ቁልፍ ቃላት

ማስተናገድ፡- ዘርፈ ብዙ ልዩነቶች ፍቅዶና ተቀብሎ መኖር

ብዝሃነት፡- በተለያዩ መስፈርቶች ምክንያት በሰዎች የሚታይ ልዩነት

ብሄር፡- የአንድ የተወሰነ ማህበራዊ ቡድን

ሰርግ፡- ሁለት ሰዎች በትዳር ውስጥ የሚዋሀዱበት ሥነ-ሥርዓት።

የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ መልመጃ ጥያቄዎች

ክፍል አንድ፡ የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እዉነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት ጻፉ።

1. ብዝሃነት በተለያዩ ቡድኖች መካከል ያለ ልዩነት ነዉ፡፡
3. ባህል እና ማህበረሰብ የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡
4. ባህል የሌለው ማህበረሰብ በአለም ላይ አለ።
5. ቋንቋ በሰዎች መካከል የመግባቢያ ሥርዓት ነው።

ክፍል ሁለት፡-በ 'ሀ' ስር የሚገኙትን ቃላት ወይም ሀረጎች በ 'ለ' ስር ካሉት ትክክለኛ የብዝሃነት መገለጫዎች ጋር አዛምዱ፡፡

'ሀ'	'ለ'
1. ከትዉልድ ትዉልድ ወረደ የአለባበስ ስርአት	ሀ. ብሄር
2. ሰዎች የሚያመልኩበት የእምነት ቡድን	ለ. የባህል ልብስ መልበስ
3. የምግብ አዘገጃጀትና አበላል	ሐ. ቋንቋ
4.የጋራ የሆነ ባህላዊ ልምዶችናእሴቶች ያሉት የሰዎች ስብስብ	መ. የባህል ሙዚቃ ሠ. የባህል ምግብ
5.ሰዎች ቋንቋን እንዲማሩ ያግዛቸዋል	ረ ሃይማኖት

ክፍል ሦስት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ

1. የባህል ብዝሃነት የሚስተናገዱበት መንገዶችን ዘርዝሩ።
2. የባህል ብዝሃነትን ማክበር አስፈላጊነቱን ግለፁ።